ULGE 02፡2022
First Edition
March 28/2022

# የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ የተሞክሮ ሰነድ
# Municipal Service Delivery Good Practice Document

መጋቢት 2014 ዓ/ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ


ክፍል አንድ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስርዓት መልካም ተሞክሮ ........ 3

ምዕራፍ አንድ ........ 3

1.1. መግቢያ ........ 4

1.2. ዓላማ ........ 5

1.3. ተሞክሮውን የመቀመር አስፈላጊነት ........ 5

1.4. መነሻ ሁኔታዎች (ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች) ........ 5

1.5. ተሞክሮ ሊወሰድባቸው የተቀመረጡ የትኩረት መስኮች ........ 7

1.6. ተሞክሮውን ለመቀመር የተሄደበት አግባብ ........ 7

ምዕራፍ ሁለት ........ 7

2.1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ዓላማ ........ 7

2.2. በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት በዝግጅት ምዕራፍ የተከናዎኑ ተግባራት ........ 7

ምዕራፍ ሶስት፡- የትግበራ ምዕራፍ ........ 9

ምዕራፍ አራት፡- የማጠቃለያ ምዕራፍ ........ 21

ክፍል ሁለት:- የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት መልካም ተሞክሮ ሠነድ ........ 22

ምዕራፍ አንድ ........ 22

1.1. መግቢያ ........ 22

1.2. ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች ........ 23

1.3. በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች የተፈቱበት አግባብ ........ 24

ምዕራፍ ሁለት ........ 26

2.1. የተተገበሩ እና ለሌሎች ተሞክሮ የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎች ........ 26

3. ማጠቃለያ ........ 48

ክፍል ሶስት፡- የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አኳያ የተከናወኑ ተሞክሮዎች ........ 50

ክፍል አንድ ........ 50

1.1. መግቢያ ........ 50

1.2. ተሞክሮውን የመቀመር አላማዎች ........ 51

1.3. ተሞክሮውን የመቀመር አስፈላጊነት ........ 52

1.4. መነሻ ሁኔታዎች/ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች ........ 52

1.5. ተሞክሮ ሊወሰድባቸው የተመረጡ የትኩረት መስኮች /ወሰን/ ........ 53

1.6. ተሞክሮውን ለመቀመር የተሄደበት አግባብ ........................................................................ 53

ክፍል ሁለት፡- የዝግጅት ምዕራፍ ........................................................................ 53

ክፍል ሦስት፡- የትግበራ ምዕራፍ ........................................................................ 55

3.1. የከተማዋ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ትግበራ ሂደትና የተገኙ ውጤቶች/ተሞክሮዎች ........................................ 55

3.2. በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ........................................................................ 56

3.3. ያጋጠሙ ችግሮች የተፈቱበት አግባብ ........................................................................ 57

ክፍል አራት፡- የማጠቃለያ ምዕራፍ ........................................................................ 59

4.1. የመልካም አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን በመፍታት ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ የመፍጠሩ ሁኔታ ቀጣይነት ያለው ስለመሆኑ ........................................................................ 59

4.2. ተሞክሮውን ለአቻ ከተሞች /ተቋማት ለማስፋት የተሄደበት ርቀት ........................................ 60

4.3. ማጠቃለያ ........................................................................ 60

## ክፍል አንድ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስርዓት መልካም ተሞክሮ

## ምዕራፍ አንድ

## 1.1. መግቢያ

አዲስ አበባ ከተማ የአፍሪካ ህብረት፣ የተለያዩ ኢምባሲዎች፣ ዲፕሎማቶች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መቀመጫ እና የሀገሪቱ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማዕከል ስትሆን ከተማዋን ጽዱና ውብ በማድረግ ለነዋሪዎቿና ለእንግዶቿ ምቹና ተመራጭ ለማድረግ የከተማው አስተዳደር ለጽዳቱ ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት ውጤታማ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ለዚህም ማሳያ የጽዳት አስተዳደር ዘርፍ የነበረበትን የአደረጃጀትና የሰው ኃይል ችግር ሙሉ በሙሉ የሚቀርፍ መዋቅራዊ አደረጃጀት (BPR) በማስጠናት ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን በዘርፉ የነበረበትን የሰው ኃይልና አደረጃጀት በመፍታት ለህብረተሰቡ ፈጣንና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጥ እያደረገው ይገኛል፡፡ በዘርፉ ለተመደበው የሰው ኃይልም የደህንነት መጠበቂያ፣ የንጽህና መጠበቂያ፣ ትርፍ ሰዓት፣ የሽታ አበል፣ ለመንገድ ጽዳት ሰራተኞች ነጻ የአውቶብስ ትኬት ወዘተ ሌሎችንም ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡

ጽዳት ህዝባዊ መሰረት ከሌለው ውጤታማ እንደማይሆን በመረዳት ከዚህ በፊት በየወሩ ሲደረግ የነበረን የጽዳት ንቅናቄ ቋሚ ሳምንታዊ የጽዳት ንቅናቄ እንዲሆን በማድረግ ከላ እስከ ታች ያለው አመራር በባለቤትነት እንዲመራው በማድረግ እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ክፍት ቦዮች ጠረጋና የወንዝ ዳርቻ ጽዳት በማከናወን የከተማው ጽዳት እንዲሻሻል ማድረግ ተችሏል፡፡

ከደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማጓጓዝ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት መንግስት ሲያጓጉዘው የነበረውን ደረቅ ቆሻሻ አውትሶርስ በማድረግ በግል ድርጅቶች እንዲጓጓዝ ማድረግ፣ ጊዜያዊ የቅብብሎሽ ጣቢያዎችን በመገንባት፣ የሸርክና ማህበራትን በጋሪ ከመሰብሰብ ወደ በተሽከርካሪ እንዲሰበስቡ የማድረግ፣ ከተማዋ ከገንዳ ቆሻሻ የመሰብሰብ ስርዓት እንድትወጣ በማድረግ፣ የመንገድ ጽዳት ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ ውጤታማ ተግባር እየተከናወነ ይገኛል፡፡

የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎችን በልዩ ትኩረት በመስራት ዘርፉ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠሪያ እንዲሆን የማድረግ፣ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎቻችን ውጤታማ እንዲሆኑ ኮምፖስት ለሚያመርቱና ወረቀት ለሚሰበስቡ ማህበራት ማበረታቻ ድጎማ በመፍቀድ፣ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ኤግዚቢሽን በማዘጋጀት በየአመቱ በዘርፉ የተሰማሩ ዜጎች በመቶ ሚሊዮን ብር እንዲያገኙ እየተደረገ ሲሆን ቆሻሻ የውጭ ምንዛሬ ማስገኛ ዘርፍም እየሆነ ይገኛል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ ዘመናዊ ላንድፊል የሌላትና ከዚህ በፊት ቆሻሻ እየተደረመሰ የዜጎቻችንን ህይወት ሲያጠፋ የነበረውን ረጲ ማስወገጃ ቦታ የጃፓንን ፉኩካ ቴክኖሎጂን ተግባራዊ በማድረግ የቆሻሻ መደርመስን በማስቀረት በማስወገጃ ቦታው የሚከሰትን ብክለትን ለመቀነስ ውጤታማ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ አጠቃላይ የጽዳትና ውበት ስራዎችን በተቀናጀና ህዝባዊ ተሳትፎን ባረጋገጠ መልኩ ተካሂዶ አስተማማኝ ውጤት እንዲመዘገብና ያሉንን እሴቶች ቀጣይነት ለማረጋገጥ እንዲቻል በህብረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ፣ በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ፣ የቅብብሎሽ ጣቢያ ግንባታና የማስወገጃ ቦታ አስተዳደር ላይ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች ተቀምሮ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 1.2. ዓላማ

### 1.2.1. ጥቅልዓላማ

በህብረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ፤ በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፤ አጓጓዝ፤ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ፤ በቅብብሎሽ ጣቢያ ግንባታ እና የማስወገጃ ቦታ አሰራር ላይ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን ለሌች ትምህርት ሊሆን በሚችል መልኩ በመቀመር እንዲሰፋ ማድረግ፡፡

### 1.2.2. ዝርዝር ዓላማ

ሀ/ በህብረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ የተገኙ መልካም ውጤቶችን ለሌሎች ትምህርት በሚሆን መንገድ መቀመር፤

ለ/ በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ዘርፍ የታዩ መልካም ተሞክሮዎችን መቀመር፤

ሐ/ በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማጓጓዝ የሚገኙ ተሞክሮዎችን መቀመር፤፤

መ/ የጊዜያዊ ቅብብሎሽ ጣቢያ ግንባታ ተሞክሮዎችን መቀመር፤

ሠ/ በማስወገጃ በታ የሚታዩ መልካም ተሞክሮዎችን ለሌሎች ትምህርት በሚሆን መንገድ መቀመር፤

## 1.3. ተሞክሮውን የመቀመር አስፈላጊነት

አዲስ አበባ ከተማ ከጥቂት ዓመታት በፊት ከፍተኛ የጽዳት ችግር የሚታይባት፤ በየመንገዱ፤ በወንዝ ዳርቻዎችና ክፍት ቦታዎች ላይ ደረቅ ቆሻሻ የሚጣሉበት፤ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎች በኢ-መደበኛ ብቻ የሚከናወኑባት፤ የህብረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎች ዝቅተኛ የነበሩባት፤ ደረቅ ቆሻሻ በገንዳ በማከማቸት ከፍተኛ የህብረተሰብ ቅሬታ የሚቀርብባት ከተማ ነበረች፡፡ ይህንን ችግር በመፍታት ከተማዋን ጽዱና ለነዋሪዎቿና ለእንግዶቿ ምቹ የመኖሪያና የሥራ ከተማ ለማድረግ በርካታ ተግባራት በመንግስትና በህብረተሰቡ ቅንጅት እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ ይህ ቅንጅታዊ ስራ ውጤት አፍርቶ ከተማዋ ዛሬ በተሻለ የጽዳት፤ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ፤ የህበረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎች ላይ አመርቂ ውጤት በማስመዝገብ ጽዳቷ እየተሻሻለ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ይህንን ውጤት ለሌሎችም ከተሞች ተሞክሮ ሊሆን በሚችል መልኩ ቀምሮ ማስቀመጥና ወደ ሌሎች ከተሞችም ማስፋት አስፋላጊ በመሆኑ ተሞክሮውን መቀመር አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡

## 1.4. መነሻ ሁኔታዎች (ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች)

### 1.4.1. ከመዋቅራዊ አደረጃጀት አንጻር

የአዲስ አበባ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በከተማው የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለው መዋቅራዊ አደረጃጀትም ይሁን የሰው ኃይል ያልነበረው እና ከኤጀንሲ እስከ ወረዳ በአንድ ስራ ሂደት ብቻ ተደራጅቶ የቆየ በመሆኑ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ አሉታዊ አስተዋጾ ሲያደርስበት ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ የተሰማራው የሰው ኃይል የደህንነትና የንጽህና መጠበያ ግብዓት እና ሌሎችም ጥቅማጥቅሞች ያልተሟሉለት በመሆ የቅሬታ ምንጭ ሲሆን ቆይቷል፡፡

### 1.4.2. ከህብረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎች አንጻር

በከተማችን አዲስ አበባ የጽዳት ንቅናቄና የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራዎች ወጣ ገባ የበዛበት፤ በየደረጃው የሚገኘው አመራርም ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ያልያዘው፤ በየወሩ ሲካሄዱ የነበሩ ንቅናቄዎችም ብዙም ውጤት ያላመጡበትና ህብረተሰቡም በስፋት ተሳታፊ ያልነበረበት፤ የህበረተሰቡ የግንዛቤ አሰጣጥ ስራዎቻችን ተደራሽ ያልነበረበት መሆኑ፤

### 1.4.3. ከደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማጓጓዝ አንጻር

ከቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ የማሰባሰብና የማጓጓዝ አቅም ከ75 ፐርሰንት ያልዘለለ የነበረበት፤ ደረቅ ቆሻሻ ከቤት ለቤት የሚሰበስቡ ሁሉም ማህበራት ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡት በጀርባቸው፤ በጭንቅላታቸውና በጋሪ የነበረ በመሆኑ ከቤት ለቤት ቆሻሻ መሰብሰብ ተደራሽነት ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረጉ፡፡ በከተማዋ የደረቅ ቆሻሻ ማሰባሰብና ማጓጓዝ አገልግሎት በገንዳ ስርዓት የሚሰጥ የነበረ በመሆኑ ለትራፊክ ፍሰት ችግር የሚፈጥር መሆኑ፤ ገንዳው ቶሎ ስለሚሞሉና የመያዝ አቅሙ ዝቅተኛ ከመሆኑ ጋር ተደምሮ ቆሻሻው በወቅቱ ስለማይነሳ የቅሬታ ምንጭና አካባቢውም እንዲበከል ማድረጉ፤ የመንገድ ጽዳት ስታንዳርድ የሌለውና በወረዳ 20 ሰው ብቻ በመዋቅር የተመደበ የነበረ በመሆኑ የከተማውን የመንገድ ጽዳት ለማከናወን አስቸጋሪ የነበረ፤ በማህበራት ከቤት ለቤት የተሰበሰበ ደረቅ ቆሻሻ በመንግስት ተሽከርካሪ ለማጓጓዝ የተለያዩ ተግዳሮቶች ያጋጥሙ የነበረ መሆኑ፤

### 1.4.4. ከመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ አንጻር

በአዲስ አበባ ከተማ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎች በኢ-መደበኛ (በቆራሊዮ) እና በማስወገጃ ቦታ በሚገኙ ጫሪዎች ብቻ የተወሰኑ ግብዓቶች የሚሰበሰቡ በመሆኑ በከተማ ደረጃ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ከ3% የዘለለ አለመሆኑ፤ በከተማው ከ60% በላይ የሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ የሚያመነጭ ቢሆንም በኮምፖስት ማምረትና መጠቀም ዙሪያ የነበረ እንቅስቃሴ ዝቅተኛ መሆኑ፤ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረጊያ ቦታ የተመቻቸ ያልነበረ መሆን፤

### 1.4.5. የጊዜያዊ ማቆያ ቦታ ግንባታ አንጻር

አዲስ አበባ ከተማ በማስተር ፕላን የተካለለ የጊዜያዊ ማቆያ ቦታ የሌላት በመሆኑ የጊዜያዊ ቆሻሻ ማስቀመጫ ቦታዎች በአብዛኛው በግለሰቦችና ድርጅቶች አጥር አጠገብ፤ ወንዝ ዳርቻና ክፍት ቦታዎች ላይ ሲቀመጡ የነበረ መሆኑ፤ በተለይ የገንዳ ማስቀመጫዎች በነዋሪው ህረተሰብ አጠገብና በመንገድ ዳር ሲቀመጡ የነበሩ በመሆኑ በከተማው ነዋሪ ህብረተሰብ ቅሬታ ሲፈጥር ቆይቷል፡፡

### 1.4.6. ከማስወገጃ ቦታ አንጻር

አዲስ አበባ ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሌላት ሲሆን በዚህም ምክንያት በተደጋጋሚ ቆሻሻ እየተደረመሰ የሰው ህይወት ሲያጠፋ ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም ከማስወገጃ ቦታ የሚወጣው ሽታና ፍሳሽ በአካባቢ ላይ ብክለት በማስከተል በአካባቢው ነዋሪ ቅሬታ ሲፈጥር ቆይቷል፡፡

## 1.5. ተሞክሮ ሊወሰድባቸው የተቀመረጡ የትኩረት መስኮች

i. የህብረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎች፤

ii. የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ተግባራት፤

iii. ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ ስርዓት፤

iv. የጊዚያዊ ቆሻሻ ማቆያ ቦታ ግንባታና ቅንጅታዊ አሰራር

v. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ አስተዳደር

## 1.6. ተሞክሮውን ለመቀመር የተሄደበት አግባብ

- ተሞክሮ ከመቀመሩ በፊት ኮሜቴ ተደራጅቶ ተሞክሮ ሊሆኑ የሚችሉ የትኩረት መስኮች የመለየት ስራ ተሰርቷል፤
- የመስክ ጉብኝት በማድረግ ተግባሩን በተጨባጭ የማየትና መረጃዎችን በምስል፤ በፎቶ የመያዝ ስራ ተሰርቷል፤
- በእያንዳንዱ የትኩረት መስክ ነባራዊ ዳሰሳ ተደርጓል፤
- በአገልግሎት አሰጣጡ የማህበረሰቡ እርካታ ዳሰሳ ተደርጓል፤

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ዓላማ

የአዲስ አበባ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ አላማ በከተማው የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ደረቅ ቆሻሻ በተገቢው ሁኔታ በመሰብሰብ፤ በማጓጓዝ፤ መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግና ምንም ጥቅም የማይሰጠውን ደረቅ ቆሻሻ በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት ሳያስከትል እንዲወገድ በማድረግ ጽዱ ከተማ መፍጠር የሚል ነው፡፡

## 2.2. በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት በዝግጅት ምዕራፍ የተከናዎኑ ተግባራት

i. **አጠቃላይ በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን ዳሰሳ ማድረግ፡-** የአዲስ አበባ ከተማን የጽዳት አገልግሎት ችግርን በዘላቂነት ለመፍታት ያስችል ዘንድ አጠቃላይ በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን ዳሰሳ በማድረግ የመፍትሄ መንገዶች እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

ii. **የማስፈጸሚያ እቅድ ማዘጋጀት፡-** የተለዩ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉበትን የመፍትሄ አቅጣጫዎች መሰረት በማድረግ የተለያዩ የማስፈጸሚያ እቅዶች በተለያየ ጊዜ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ የዴሊቨሪ እቅድ፣ የፈጣን ምላሽ እቅድና ልዩ የጽዳት ንቅናቄ እቅድ ወዘተ፡፡

iii. **ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ መግባያ ሰነድ መፈራረም፡-** እቅዱን መሰረት በማድረግ ከተለያዩ ባለድርሻ አካለት ጋር በቅንጅት መስራት እንዲቻል እቅዱን የጋራ ማድረግና ከወሳኝ ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ወደ ተግባር እንዲገባ ማድረግ፡፡

iv. **ድጋፍ የሚያደርጉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ማሳተፍ፡-** ለእቅዱ ውጤታማነት አጋዥ የሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እገዛ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

v. **መመሪያዎችንና ስታንዳርዶችን ማሻሻል ወይም አዳዲሶችም እንዲወጡ ማድረግ፡-** ለአሰራር እንቅፋት የነበሩና ከጊዜው ጋር ሊሄዱ የማይችሉ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች እንዲከለሱ የተደረገ ሲሆን አዳዲስ አሰራሮችን ሊያስተገብሩ የሚችሉ አዳዲስ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች እንዲዘጋጁ ተደርገዋል፡፡

vi. ከአደረጃጀትና ከሰው ኃይል ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን አዲስ BPR እንዲጠና ማድረግ፤

vii. በአመራሩና በፈጻሚው የሚታየውን የአመለካት ችግር ለመፍታት ግምገማነክ ስልጠናዎችን በዘርፉ ላለው መዋቅር በሙሉ እንዲወስድ ማድረግ፤ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን የማመቻቸት ተግባር ተከናውኗል፤

viii. ማስፈጸሚያ እቅዶችን በየደረጃው የሚገኘው አመራር ፈርሞ እንዲረከብና ባለቤት እንዲሆን ማድረግ፤

ix. ከነዋሪው ህብረተሰብ ጋር በየደረጃው የውይይት መድረኮችን ማመቻቸት

x. የጽዳት አምባሳደሮችን በመሰየም ንቅናቄውን እንዲያስተባብሩ የማድረግ፤


xi. ከፍተኛ አመራሩ ትኩረት እንዲሰጠው ጉብኝቶችን በማመቻቸት ችግሮችን የማስገንዘብ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት፡- የትግበራ ምዕራፍ

## 3.1. በትግበራ ሂደትና የተገኙ ውጤቶች (ተሞክሮዎች)

### 3.1.1. ከተቋም መዋቅራዊ አደረጃጀትና የሰው ኃይል

- የከተማው አስተዳደር ለጽዳትን ልዩ ትኩረት በመስጠት አዲስ አደረጃጀት (BPR) በማጽደቅ በዘርፉ የነበረው የአደረጃጀትና የሰው ኃይል ችግር ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ እንዲቀረፍ ያደረገ ሲሆን ከዚህ በፊት በኤጀንሲ ደረጃ በአንድ ዋና ስራ ሂደት ብቻ ሲሰራ የነበረ ተግባርን በአዲሱ መዋቅር በአምስት ዋና ዳይሬክቶሬት እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡
- በክፍለ ከተማና ወረዳ ደረጃ በጥቂት ባለሙያ ብቻ ተደራጅቶ የነበረውን የጽዳት ጽ/ቤት አሁን ላይ በሶስት ቡድኖችና በበቂ የሰው ኃይል እንዲደራጅ ማድረግ ተችሏል፡፡
- ከዚህ በፊት በመንገድ ጽዳት በወረዳ 20 ሰው አጠቃላይ በከተማ ከ2,300 የማይበልጥ የነበረን የሰው ኃይል አሁን ላይ በአዲሱ አደረጃጀት ከ11,799 በላይ መደብ በማስፈቀድ መንገዶች በስታንዳርዳቸው እንዲጸዱ እየተደረገ ይገኛል፡፡
- JEG ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ለጽዳት ዘርፍ ልዩ የደሞዝ ስኬል ተግባራዊ በማድረግና ሰራተኛ የደህንነት መጠበቂያ፤ ትርፍ ሰዓት፤ የሽታ አበል፤ የወተት አበል፤ ለመንገድ ጽዳት ሰራተኞች ነጻ የአውቶብስ ትኬት፤ ማስወገጃ ቦታ ለሚሰሩ ሰራተኞች ልዩ የአትክልት ክፍያ ወዘተ ተግባራዊ በማድረግ በዘርፉ የሚገኘው ባለሙያ ስራውን በተነቃቃ መንፈስ እንዲያከናውን አድርጎታል፡፡




**ስዕል1፡- አዲሱ የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የአደረጃጀት መዋቅር**

### 3.1.2. የህብረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎች

- "አካባቢዬን በማጽዳት ለከተማዬ ውበት አምባሳደር ነኝ" በሚል መሪ ቃል ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ሳምንታዊ ቋሚ የጽዳት ንቅናቄ ተግባራዊ በማድረግ ህገ-ወጥ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎችን፣ ክፍት ቱቦዎችን፣ የወንዝ ዳርቻዎችንና ድልድዮችን በማጽዳት የከተማው ጽዳት እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡




**ስዕል 2፡-** የንቅናቄ ማስጀመሪያ ፕሮግራም

- ከላይ እስከ ታች ያለው አመራር ለጽዳት ንቅናቄው ልዩ ትኩረት በመስጠቱ የከተማዋ ከንቲባን ጨምሮ ከፍተኛ አመራሮች፣ ሚኒስትሮችና የክፍለ ከተማና ወረዳ ስራ አስፈጻሚዎች በየሳምንቱ በየንቅናቄው መድረክ በመሳተፍና ንቅናቄውን ቀጣይነት ያለውና ውጤታማ እንዲሆን አድርጎታል፡፡



**ስዕል 3፡-** የአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ አመራሮች በጽዳት ንቅናቄ ላይ

- ታዋቂ ሰዎችን፣ አርቲስቶችን፣ ምሁራንን፣ የስፖርት ክለብ ደጋፊዎችን፤፣ የእምነት አባቶችን፣ ባለሀብቶችን፣ ወጣቶችን ወዘተ በመለየት የጽዳት አምባሳደር ሆነው ህብረተሰቡን እንዲቀሰቅሱና እንዲያስተባብሩ እውቅና በመስጠት በተሰራ ውጤታማ ተግባር በየሳምንቱ ከ500,000 ሰው በላይ በጽዳት ንቅናቄው እንዲሳተፍ ማድረግ ተችሏል፡፡








**ስዕል 4፡- የጽዳት አምባሳደር እውቅናና በጽዳት ስራ ላይ**

- በየሳምንቱ ዓርብ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ የፖሊስና መከላከያ ሰራዊት፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ወዘተ ተሳታፊ እንዲሆኑ በታቀደው እቅድ መሰረት አብዛኛዎቹ ተቋማት ተሳታፊ በመሆን አካባቢያቸውን ጽዱ ማድረግ ችለዋል፡፡




**ስዕል 5፡-**የተለያዩ ተቋማት በጽዳት ንቅናቄ ላይ

- በከተማ የሚገኙ ***ህገወጥ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎችን፣ የወንዝ ዳርቻዎችንና ክፍት ቱቦዎችን*** በመለየት በየሳምንቱ በሚካሄድ የጽዳት ንቅናቄ እንዲጸዱ በመደረጉ የህገወጥ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎችን መቀነስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የጽዳት ንቅናቄው ብሎክን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የከተማው ጽዳት እንዲሻሻል ጉልህ አስተዋጾ ያበረከተ ሲሆን በገንዘብ ሲተመንም ከ237,446,550 ብር በላይ ህብረተሰቡ በጉልበቱ አስተዋጾ አበርክቷል፡፡




**ስዕል 6፡**

- ... ዊ ልዩ የክረምት ... ቻዎችንና ክፍት ቱቦዎችን ጽዱ የማድረግ ተግባር ተከናውኗል፡፡
- በህብረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄና ግንዛቤ ስራዎቻችን በከተማው የሚገኙ በርካታ ብሎኮች ጽዱና ሞዴል መሆን ጀምረዋል፤ አጠቃላይ ህብረተሰቡም በጽዳት ለውጥ መምጣቱን መመስከር ጀምሯል፣ እንዲሁም ከዚህ በፊት በዘርፉ ሲቀርብ የነበረ የህብረተሰብ ቅሬታ መቀነስ ችሏል፡፡

**ስዕል 7፡-**በጽዳት ሞዴል ብሎክ

### 3.1.3. ውጤታማ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ተግባራት

#### ሀ. የመልሶ መጠቀምና ዑደት ማድረግ መጠንን ማሳደግ

በአዲስ አበባ ከተማ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ አገልግሎት የሚውለው የደረቅ ቆሻሻ በ2009 ዓ.ም 14,000 ቶን ብቻ የነበረው በአሁኑ ወቅት በዓመት ከ50,000 ቶን በላይ ቆሻሻ ጥቅም ላይ እየዋለ ሲሆን በዚህም በዓመት ከ141,354,651 ብር በላይ በዘርፉ የተሰማሩ ዜጎች ገቢ በማግኘት ላይ ናቸው፡፡ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራ በዓመት ከ8,000,000 ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት እየቻለ ይገኛል፡፡

| ተ.ቁ | ዓይነት | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም | 2011ዓ.ም | 2012 ዓ.ም | 2013 ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጥቅም ላይ የዋለ ቆሻሻ በቶን | 14,584 | 23,365 | 30321 | 35,727 | 49,722 |
| 2 | በሀገር ውስጥ ቆሻሻ ተሸጦ የተገኘ በብር | 36,066,200 | 61,869,000 | 84,643,000 | 99,267,299 | 141,354,651 |
| 3 | የተገኘ ውጭ ምንዛሬ በዶላር | 1,000,000 ዶላር | 1,2000,000 ዶላር | 1,700,000 ዶላር | 3,600,000 ዶላር | 8,000,000 ዶላር |

**ሰንጠረዥ 1፡-**የመልሶ መጠቀም እድገት የሚያሳይ

#### ለ. በስራ እድል ፈጠራ የተገኘ ውጤት

የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ተግባር በዘርፉ የስራ እድል መፍጠሪያ እየሆነ የመጣ ሲሆን በ2009 በዘርፉ የተፈጠረ የስራ እድል የሌለ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ከ4,000 በላይ የሚሆኑ ዜጎች በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ዘርፍ በማህበር ተደራጅተው የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው ማድረግ ተችሏል፡፡

#### ሐ. የወረቀትና ኮምፖስት ስራ ውጤታማነት

በስራ እድል ፈጠራ በኮምፖስት ዝግጅት ለተደራጁ ማህበራት ለኮምፖስት ማምረት የሚሆን ደረቅ ቆሻሻ ከአትክልት ተራ በማቅረብ፤ የተለያዩ ግብዓትና የተግባር ስልጠና በመስጠት፤ የስራ ቦታ በማመቻቸት ለተመረተ ኮምፖስት ከተፋሰስና አረንጓዴ ልማት ከተደራጁ ማህበራት ጋር በማስተሳሰር ከሁለት ዓመት በፊት በከተማው በመደበኛነት የሚመረት ኮምፖስት የሌለ

ሲሆን አሁን ላይ በኮምፖስት በተደራጁ ማህበራት ብቻ በዓመት ከ1,000 ቶን በላይ ኮምፖስት በማምረት እንዲሸጥ ማድረግ ተችሏል፡፡





**ስዕል 8፡-** በኮምፖስት የተደራጁ ማህበራት የሚመረት ኮምፖስት

የወረቀት መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎችን በማሳደግ የወረቀት ደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ መጠንን ለማሳደግ በወረቀት መሰብሰብ ዘርፍ ከ100 በላይ ማህበራትን በማደራጀትና መንግሳታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለእያንዳንዱ ማህበር 87 የወረቀት ማጠራቀሚያ የብረት ኮንቴይነርና የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት በማሟላት ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በዚህም የወረቀት መሰብሰብ አቅም በ2009 ዓ.ም በዓመት 300 ቶን የነበረ ሲሆን አሁን ላይ መጠኑ አድጎ በወር ከ600 ቶን በላይ ወረቀት እየተሰበሰበ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት እንዲውል ማድረግ ተችሏል፡፡



**ስዕል 9፡-** በድጋፍ የተሰራ የወረቀት ማጠራቀያ

## መ. የማበረታቻ ክፍያ ስርዓት አተገባባር

- በከተማዋ የሚመረተውን የኮምፖስት ገበያ ችግርን በዘላቂነት ለመፍታትና የመንግስት ተቋማት ኮምፖስት ያለጨረታ እንዲገዙ ለማድረግ ጥናት በማጥናት የአንድ ኪሎ ግራም የኮምፖስት ቁርጥ ዋጋ ብር 4.00 (አራት ብር) በፋይናንስ ቢሮ በኩል በማጸደቅ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡
- በወረቀትና ኮምፖስት የተደራጁ ማህበራትን ለማበረታታት የከተማው አስተዳዳር ወረቀት ሰብስበው ለሚሸጡ ማህበራት ብር 1.50 (አንድ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) እንዲሁም ኮምፖስት አምርተው ለሚሸጡ ማህበራት በኪሎ ግራም ብር 3.00 (ሶስት ብር) የማበረታቻ ድጎማ ክፍያ አጸድቆ ተግባራዊ አድርጓል፡፡

## ሠ. የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎች ኤግዚቢሽን

የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎችን ለህብረተሰቡ በማስተዋወቅ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ለመፍጠር እንዲሁም በዘርፉ ለተሰማሩ ዜጎች የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ በየአመቱ ሁሉም ክፍለ ከተማ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ኤግዚቢሽንና ባዛር እየተዘጋጀ ሲሆን በከተማ ደረጃ ከሁሉም ክፍለ ከተሞች የተውጣጡና በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶችን በማካተት ኤግዚቢሽን ማዘጋጀት ተችሏል፡፡





**ስዕል 10፡-** ኤግዚቢሽን መክፈቻ

### 3.1.4. ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ ስርዓት

#### ሀ. የደረቅ ቆሻሻ የማጓጓዝ ስራን አውትሶርስ ማድረግ

በአዲስ አበባ ከተማ ከቤት ለቤት በሽርክና ማህበራት የሚሰበሰብ ደረቅ ቆሻሻ በመንግስት ተሸከርካሪ ወደ ማስወገጃ ቦታ ሲጓጓዝበትን የነበረውን ስርዓት በጥናት በተደገፈ መንገድ የአውትሶርስ በማድረግ ቦሌ ክፍለ ከተማን ሙሉ በሙሉ የካ ክፍለ ከተማ ደግሞ በከፊል አውትሶርስ በማድረግ በተሰራ ስራ ውጤታማ በመሆኑ በቀጣይ ሶስት ዓመታት ሙሉ በሙሉ አውትሶርስ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡

#### ለ. የመንገድ ጽዳት ስታንዳርድ


- ለአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች በሶስት ደረጃ ማለትም ሶስት ሽፍት፤ ሁለት ሽፍትና አንድ ሽፍት የሚጸዱ መንገዶችን በመለየት ለእያንዳንዱ ደረጃ ስታንዳርድ በማዘጋጀት በተሰራ ስራ አሁን ላይ የመንገድ ጽዳት ሽፋን ከ99% በላይ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን ከዚህ በፊት የተለያዩ አለም አቀፍ ጉባኤዎች በከተማው ሲካሄዱ በዘመቻ ይጸዱ የነበሩ መንገዶች አሁን ላይ በስታንዳርዳቸው እየተጸዱ ይገኛል፡፡




**ስዕል 11፡-** የመንገድ ጽዳት የበፊትና የአሁን

## ሐ. ከገንዳ ስርዓት መውጣት

በአዲስ አበባ ለረጅም ጊዜ ደረቅ ቆሻሻ ሲጓጓዝ የነበረው 8 ሜትር ኩብ ብቻ በሚጭን 130 የገንዳ መኪና ሲሆን ይህም በአንድ መኪና 8 ሜትር ኩብ ቆሻሻ እያጓጓዘ የከተማውን ቆሻሻ በስታንዳርዱ መሰረት ማጓጓዝ የማይቻል በመሆኑ ከገንዳ ስርዓት በመውጣት በአንድ ጊዜ 100 ሜትር ኩብ መጫን የሚችሉ 40 ኮምፓክተር ተሸከርካሪዎች መጠቀም በመጀመራችን የማጓጓዝ አቅማችን ሲያድግ የተሸከርካሪ ወጭን እንዲቀንስ ማድረግ ተችሏል፡፡




**ስዕል 12፡-** የገንዳ መኪና ወደ ኮምፓክተር ሽግግር

## መ. ከቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡ ማህበራት

ከቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡ ማህበራት ከአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ጋር ብድር በማመቻቸት እንዲሁም 20 ፐርሰንት ቁጠባ እንዲቆጥቡ በማድረግ በጀርባቸውና በጋሪ ቆሻሻ ሲሰበስቡ የነበሩ ማህበራት አሁን ላይ ከ165 በላይ አነስተኛ መኪና ገዝተው ቤት ለቤት ቆሻሻ መሰብሰብ በመጀመራቸው ማህበራቱም ውጤታማ ሲሆኑ የመሰብሰብ አቅማቸውም ወደ 99 ፐርሰንት ማደግ ችሏል፡፡ በአሁኑ ሰዓት እነዚህ ማህበራት ከ50,000,000.00 ብር በላይ በአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ውስጥ አስቀምጠዋል፡፡



**ስዕል 13፡-** የማህበራት እድገት

### 3.1.5. የቅብብሎሽጣቢያ ግንባታ ትግበራ

- አዲስ አበባ ከተማ በማስተር ፕላን የተመላከተ ጊዜያዊ ማቆያ ቦታ የሌላት ሲሆን በዚህም ምክንያት የቆሻሻ ማስቀመጫዎች በመኖሪያና መንገድ ዳር በመሆናቸው ከፍተኛ የህብረተሰብ ቅሬታና የከተማዋን ገጽታ እያበላሸ ይገኛል፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት በሁሉም ክፍለ ከተሞች ለሁሉም ሽርከና ማህበራት 500 ካ.ሜ ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ቅብብሎሽ ማዕከል ግንባታ በመንግስት በጀት የተጀመረ ሲሆን  አሁን ላይ 11 ተጠናቀዋል፡፡ ይህም የከተማዋን ገጽታ እያሻሻለው ይገኛል፡፡

ግንባታው የተጠናቀቀ

ቀደም ሲል የነበረ







**ስዕል 14፡-** የተጠናቀቀ ጊዚያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ማዕከል

## 3.1.6. ደረቅ ቆሻሻን በተገቢው ሁኔታ ማስወገድ

### ሀ. የማስወገጃ ቦታ ኦፕሬሽን

አዲስ አበባ ከተማ በማስወገጃ ቦታ ችግር ምክንያት የቆሻሻ መደርመስን ለመከላከል እንዲሁም በየቀኑ የሚመነጭን ከ2500 ቶን በላይ ደረቅ ቆሻሻ ከ60 ዓመታት በላይ አገልገሎት እየሰጠ በሚገኘው የማስወገጃ ቦታ በተገቢው ሁኔታ ለማስወገድ የተለያዩ 12 ማሽነሪዎችን በመጠቀም አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡





**ስዕል 15፡-** በማስወገጃ ቦታ የሚገኙ ማሽነሪዎች

## ለ. የፉኩካ ተሞክሮ

በማስወገጃ ቦታ ሲከሰት የነበረን የቆሻሻ መደርመስ አደጋ ለመከላከል ያስችል ዘንድ የጃፓን ፉኩካ ቴክኖሎጂ ተሞክሮ በማስፋት በማስወገጃ ቦታው **12 ሄ/ር** በጋቢዮን የተደገፈ እርከን ስራ ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በማስወገጃ ቦታ **65%** የሚመነጨውን ሜቴን ($CH_4$) ጋዝ የተለያዩ ፓይፖችን ማለትም 2 ሜትር ቁመት አራት በአራት ጉድጓድ ተቆፍሮ 50 ሳንቲ ሜትር በድንጋይ ከፍታ በመስራት ***በ1.5 ሜትር*** ላይ ፓይፕ በመትከልና ዙርያውን በድንጋይና በበርሜል እንዲሸፈን በማድረግ ከውጭ እና ከውስጥ የአየር ዝውውርን በመፍቀድ ማስወገጃ ቦታ እንዲረጋጋ ማድረግና በዋናነት ሚቴን ጋዝን ወደ ካርቦንዳይኦክሳይድ በመቀየር ለዓለም የሙቀት መጠን መጨመር 20 እጥፍ አደጋ የሆነውን ሜቴን ጋዝ እንዲቀንስ ማድረግ እየተደረገ ነው፡፡ እንዲሁም በማስወገጃ ቦታ የሜቴን ጋዝ መጠን ከ65- 75 ዲግሪ በላይ ሆኖ በከፍተኛ ሙቀት ሳቢያ ሊከሰት የሚችለውን እሳት ከመቆጣጠርም ረገድ ያለው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በአብዛኛው የመደርመስ አደጋን ማስቀረት ተችሏል፡፡





**ስዕል 16፡-** የላንደፊል ፉኩካ ተሞክሮ እና የጋዝ ማስተንፈሻ ፓይፕ ስራ

# 3.2 በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

## ሀ. ውጫዊ ችግሮች

- ማሽነሪዎችንና ተሽከርካሪዎችን ከውጭ ለማስገባት የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት፣
- በማህበራት የተመረተ ኮምፖስት የገበያ ችግር፣
- የጊዜያዊ ማቆያ ጣቢያዎች የቦታ አቅርቦት ችግር፣
- የግንባታ መጓተት፡፡

## ለ. ውስጣዊ ችግሮች

- የባለሙያው አመለካከትና የአቅም ውስንነት፣
- ተግባራትን በእኩል መፈጸም አለመቻል፡፡

## 3.3 ያጋጠሙ ችግሮች የተፈቱበት አግባብ

- የማሽነሪዎች ብልሽት ሲያጋጥም በኪራ ይመጠቀም፣
- ለዘርፉ ባለሙያ ተከታታይነት ያለው ስልጠና መስጠት፣
- ከግንባታ መጓተት ጋር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ተደጋጋሚ ውይይት ማድረግ፣
- የኮምፖስት ገበያ ችግርን ለመቅረፍ ከተፋሰስና አረንጓዴ ልማት ከተደራጁ ማህበራት ጋር ማስተሳሰር፡፡

## ምዕራፍ አራት፡- የማጠቃለያ ምዕራፍ

## 4.1. የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ትግበራ ቀጣይነት ያለው ስለመሆኑ

በየደረጃው የሚገኘው ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥ ቀጣይነት እንዲኖረው የማድረግ ተግባራት የተከናወነ ሲሆን

- ዘርፉ ከማዕከል እስከ ወረዳ በተሟላ የሰው ሃይል የተደራጀ በመሆኑ ቀጣይነት ባለው ክትትልና ድጋፍ የሚመራ ይሆናል፡፡
- የጽዳት ንቅናቄና የህብረተሰብ ስራ ቀጣይነት እንዲኖረው ብሎክን መሰረት ያደረገ ልዩ የጽዳት ንቅናቄ እቅድ ተዘጋጅቶ ከመጋቢት 03/2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ለማድረግ ከብሎክ ተወካዮችና ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካለት ጋር እቅድ ውይይት ተደርጓል፡፡
- የጽዳት ንቅናቄ ስራዎችና የግንዛቤ ስራዎቻችን ቀጣይነት እንዲኖራቸው በብሎክ ደረጃ ለወረዳ ባለሙያ ብሎክ በማስረከብ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡
- የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎች ቀጣይነት እንዲኖራቸው የማበረታቻ ድጎማ እየተሰጠ ይገኛል፡፡
- አውትሶርስን በሁሉም ክፍለ ከተማዎች ተግባራዊ ለማድረግ በእቅዱ መሰረት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

## 4.2. ተሞክሮውን ለአቻ ተቋማት ለማስፋት የተሄደበት ርቀት

- ከተለያዩ የክልል ከተሞች ለሚመጡ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘርፍ ተሞክሮውን የማጋራት እንዲሁም ለተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች መረጃውን በመስጠት እንዲሰፋ የማድረግ ተግባራ ተከናውኗል፡፡

## 4.3. ማጠቃለያ

### 4.3.1. ትምህርት ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

### ሀ. በጥንካሬ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችና ትምህርቶች

- ቅንጅታዊ አሰራር ጠንካራ መሆን፡- የጽዳት ስራ የአንድ ተቋም ተግባርና ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ባለድርሻ አካለት ቅንጅትን የሚጠይቅ ሲሆን የመንገድ ዳር ቱቦዎችንና የወንዝ ዳርቻዎችን ከመንገዶች ባለስልጣንና ከተፋሰስና

አረንጓዴ ልማት ቢሮ ጋር በመቀናጀት የጋራ እቅድ በማዘጋጀትና በጋራ በመገምገም መስራታችን ውጤታማ አድርጎናል፡፡

- ***መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎ፡-*** ስራዎችን በመንግስት በጀት ብቻ ከመስራት ይልቅ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለዘርፉ ባለሙያዎች የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር ስልጠናዎችን እንዲሰጡ ማድረግ፤ በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ለሚደራጁ ማህበራት ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የወረቀት ማጠራቀሚያ ኮንቴይነር፣ የፕላስቲክ ጠርሙስ መጨፍለቂያ ማሽን፤ ጋሪ፤ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት፤ የተለያዩ የክህሎት ስልጠና ድጋፍ እንዲሰጡ በማድረግ በየአመቱ በሚሊዮን የሚገመት ብር ድጋፍ እያደረጉ ይገኛል፡፡
- **የአመራሩ ተሳትፎና ቁርጠኝነት፡-** በየደረጃው የሚገኘው አመራር ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠት የጽዳት ንቅናቄና ተሳትፎው ውጤታማ እንዲሆን አድርጓል፡፡
- **የክትትል፣ ድጋፍና እውቅና ስርዓት፡-** ቋሚ ክትትልና ድጋፍ ቡድን በማደራጀት ስራዎች በየጊዜው መስክ በመውረድ ድጋፍና ክትትል የተደረገበት አግባብ እና የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው የእውቅና ፕሮግራም ተዘጋጅቶ እውቅና ተሰጥቷል፡፡

# ክፍል ሁለት:- የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት መልካም ተሞክሮ ሠነድ

## ምዕራፍ አንድ

### 1.1. መግቢያ

የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት ጤናማነቱ የተረጋገጠ የእርድ አገልግሎት ለተጠቃሚው በጥራት፣ በፍጥነትና በቅልጥፍና ተደራሽ ለማድረግ የተቋቋመ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኝ መንግስታዊ የልማት ድርጅት ነው፡፡

ድርጅቱ የእርድ አገልግሎት ለተጠቃሚው ተደራሽ ከማድረግ ባለፈ ከተረፈ ስጋ የሚገኙ ግብዓቶችን ወደተረፈ ምርትነት በመለወጥ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ተረፈ ምርቶችን በማምረት ለድርጅቱ ተጨማሪ ገቢን ለማስገኘት የኢንዱስትሪ ማምረቻን ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን ከዚህ ተግባር ጎን ለጎን ሌሎች የተለያዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ገቢ እንዲጨምር እየሰራ ያለ ድርጅት ነው፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የድርጅቱ አገልግሎት አሰጣጥ አሁን ካለበት ነባራዊ ሁኔታ አንጻር በሚፈለገው ደረጃ ነው ለማለት ባያስችልም በተወሰነ መልኩም ቢሆን አዳዲስ አሰራሮችን ተግባራዊ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል ጥረት እየተደረገ አሁን ላለበት ደረጃ ደርሷል፡፡

አዳዲስ ማሻሻያ ከተደረገባቸው የአሰራር ስርዓቶች መካከል አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በድርጅቱ ተግባራዊ እንዲደረግ የተደረገበት አሰራር ዋነኛው ነው፡፡ በዚህ ሲስተም ቀድሞ የነበረውን የኮቦል አሰራር በማስቀረት በዘመናዊ አሰራር Enterprise Resource Planning (ERP) ተግባራዊ በማድረግ ተጠቃሚው በቀላሉ መረጃን እንዲያስገባና መረጃዎች በተደራጀ መልኩ ማየትና መተንተን ወደሚያስችል ደረጃ እንዲደርስ መደረጉ ትልቅ እምርታ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዛም ባለፈ ይህን ሲስተም ብቻ በመጠቀም ክፍሎችን ከክፍሎች ጋር በማገናኘት ስራዎችን መስራት የሚችሉበትን፣ አንድ ቁልፍ በመጫን ብቻ ውሳኔዎችን ማሳለፍ የሚቻልበት፣ ክፍያዎችን ማስነሳትና መፍቀድ የሚቻልበት፣ የሰው ሃይልን በተመለከተ ከፍቃድና መሰል ስራዎች ጋር ተያይዞ የሚነሱ እና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ስራዎች በቀላል መንገድ ማከናወን እና የድርጅቱን ብክነት በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ የተቻለበት ሁኔታ ጭምር የፈጠረ በመሆኑ ልዩ ትኩረት የሚያሰጠው ነው፡፡

በተጨማሪም ሌሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ጂፒኤስ፣ ሲሲቲቪ ካሜራና የሰዓት መቆጣጠሪያ አሻራ ሲስተም ከተተገበረው ሲስተም ጋር በማቀናጀት እንዲሰራ መደረጉ እና የመሳሰሉትን ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ በማድረግ እያጋጠሙ የነበሩ የስርቆትና የብልሹ አሰራር ድክመቶችን ማቆምና ማስተካከል ተችሏል፡፡ ይህም በስራው ላይ ያመጣው ለውጥ የተሻለና በቀጣይ በትኩረት ቢሰራ ከዚህ የበለጠ ለውጥ ማምጣት የሚችልበትን ሂደት የሚያሳይ ለከተማው ተሞክሮ ሊሆን የሚያስችል ነው፡፡

ስለሆነም በድርጅቱ ውስጥ ተግባራዊ የተደረጉ ቴክኖሎጂዎች ምንነት፣ የሚሰሩት ስራ እና ያመጡት ለውጥ ከዚህ በታች እንደሚከለተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡

## 1.2. ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች

ድርጅቱ ቀድሞ ይጠቀምበት የነበረው የማኑዋል ስራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ

- አብዛኛውን ጊዜ መረጃዎች በሚፈለገው ፍጥነት ማግኘት አይቻልም ነበር፡፡
- የሠነዶች የማስቀመጫ ቦታ ጥበት የነበረ በመሆኑ የሚጠፉ ሠነዶች የነበሩበት ሁኔታ የነበሩ ሲሆን በተጨማሪም ከሠነዶች መብዛት ጋር ተያይዞ ለአቀማመጥ ምቹ አለመሆን እና አይጥና መሰል ነፍሳት የሚበሉበትና ሠነዶቹ የሚበላሹበት ሁኔታ ነበር፡፡
- በተደጋጋሚ የአገልግሎት ክፍያ ሳይከፈልባቸው የእርድ አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን ድርጅቱም ማግኘት ያለበትን ገቢ በአግባቡ የማያገኝ የነበረ መሆኑ፣

- በእርድ ስራ ወቅት የእርድ አገልግሎት የተከፈለባቸው እና ያልተከፈለባቸውን ለመለየት በጣም አስቸጋሪ እና ሰፊ ጊዜን የሚወስድ የነበረ መሆኑ፣
- ለእርድ የሚቀርቡ የእንስሳት ቅበላ አሰራር ዝርክርክነት የነበረው በመሆኑ በተደጋጋሚ በከብቶች መጥፋትና መቀያየር ድርጅቱና ሠራተኛው ለከፍተኛ እዳ ይዳረጉ የነበረ መሆኑ፣
- የተመረቱ ምርቶች መረጃ በአግባቡ  የማይያዝ  በመሆኑ የምርቶች ሽያጭ በቀጥታ ወደድርጅቱ አልፎ አልፎ የማይገባበት ሁኔታ የነበረ መሆኑ፣
- በተመረቱ እና በተሸጡ የምርት ውጤቶች መካከል ያለውን የቀሪ ባላንስ ማወቅ የሚቻልበት ሁኔታ ያልነበረ መሆኑ፣
- የሰራተኞች ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታ በሰዎች በጎ ፈቃድ አማካይነት የተወሰነና ላልተገባ ዓላማ ይውል የነበረ እና ለኪራይ ሰብሳቢነት የተጋለጠ መሆኑ፣
- የጊዜያዊ ሠራተኞች ክፍያን በተመለከተ ያልነበሩ ሠራተኞች እንደነበሩ በማስመሰል ክፍያ ይፈላቸው የነበረ መሆኑ፣
- የድርጅቱ ደንበኞች የእርድ ብልት የህክምና ውጤትን ማኑዋል የሚሰራ የነበረ በመሆኑ ከደንበኞች ጋር በሚኖር አላስፈላጊ ግንኙነት የአንዱን ደንበኛ የህክምና ውጤት ለሌላው በመስጠት የማዛባት ሂደት የነበረና ከፍተኛ በመሆኑ የደንበኞች ቅሬታ የነበረ መሆኑ፣

  በመሆኑም ከላይ ከተዘረዘሩት ችግሮች በተጨማሪ ቀድሞ በርካታ ችግሮች የነበሩ ሲሆን ድርጅቱ ባደረገው ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ሽግግር አብዛኛውን ችግሮች ማስቀረት ተችሏል፡፡

## 1.3. በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች የተፈቱበት አግባብ

### 1.3.1. ውጫዊ ችግሮች

- የሚፈለጉ ቴክኖሎጂዎችን በሚፈለገው ዓይነትና ዋጋ ማግኘት ላይ የነበረ ችግር፣
- የተሻሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማግኘት ቢቻልም ከድርጅቱ አቅም ጋር የተገናዘቡ አለመሆናቸው፣
- በሀገሪቱ በቴክኖሎጂ ዘርፍ የበቁና በተግባር የበሰለ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች እና የስልጠና ተቋማት በበቂ ሁኔታ አለመኖር፣
- ኢትዮ ቴሌኮም የሚያቀርበው የመረጃ ማስተላለፊያ መስመር በየጊዜው መቆራረጥ የሚያጋጥም በመሆኑ
  - ከቅርንጫፍ ቄራው ጋር የሚደረገውን የሲስተም ትስስር ላይ ችግር መፍጠሩ፣
  - ጥሪ ማዕከሉ ወጥ ሆኖ እንዳይሰራ ተደጋጋሚ መቆራረጥ የሚያጋጥም በመሆኑ ደንበኞች አጭር የመስመር ቁጥሩን በሚፈለገው ደረጃ መጠቀም አለመቻላቸው፡፡

### 1.3.2. ውስጣዊ ችግሮች

- ሠራተኛው ራሱን በማብቃት ከተተገበረው ቴክኖሎጂ እኩል መራመድ አለመቻል፣
- ቴክኖሎጂዎች ሲተገበሩ ሠራተኛውን ይተካሉ በሚል አስተሳሰብ ለመቀበልና ተግባራዊ ለማድረግ ያለው ፍላጎት አናሳ መሆን፣
- ለቴክኖሎጂው በቂ ተጋላጭነት ባለመኖሩ በሲስተም ትግበራ ወቅት መስራት አልችልም በሚል ለትግበራው እንቅፋት መሆን፣

- ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም በሚያስፈልግባቸው የስራ መደቦች ላይ የቴክኖሎጂ ምንም ዓይነት እውቀት በሌላቸው ሠራተኞች የተያዙ መሆናቸው፣
- የተለመዱ የማኑዋል ስራዎችን ትቶ በአዲስ አሰራር በቴክኖሎጂ ለመጠቀም ያለመፈለግ፣
- የአንዳንድ ሠራተኞች የቴክኖሎጂ የመጠቀም ልምድ አለመኖር እና የቀድሞ አሰራርን በማድነቅ ቴክኖሎጂዎችን ማጣጣል፣
- አንዳንድ ሠራተኞች ሆን ብለው በቴክኖሎጂ ውጤቶች ላይ ብልሽት እንዲደርስ ማድረጋቸው፣
- የተተገበሩ ቴክኖሎጂዎች ብልሹ አሰራርን የሚያጋልጡ በመሆናቸው ስራው እንዳይተገበር ችግር ባለባቸው በአንዳንድ ሠራተኞች አማካይነት ሌሎች ሰራተኞች እንዳይቀበሉት ጥረት ማድረግ፣
- የአመራሩ የቴክኖሎጂ የእውቀት ችግር እንዳለ ሆኖ ስራውን በባለቤትነት ተቀብሎ ከመምራት ይልቅ ወደፈጻሚ በመግፋት ከፈጻሚ ጋር በመሆን አልፎ አልፎ የሚፈጠር የትግበራ ተግዳሮት፣

### 1.3.3. ችግሮቹ የተፈቱበት አግባብ

- ሠራተኞች ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ለማድረግ ተደጋጋሚነት ያለው ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ሲመጡ ከነበረው የማኑዋል ስራ ጋር ለተወሰነ ጊዜ ሠራተኛው እስኪላመድ ድረስ ጎን ለጎን እንዲሰራ ተደርጓል፡፡
- ሁሉንም ቴክኖሎጂዎች በአንድ ጊዜ ከመተግበር ይልቅ ተራ በተራ በመተግበር ሠራተኛው በተረጋጋ ስሜት እንዲላመደው ለማድረግ ተሰርቷል፡፡
- ቴክኖሎጂው ሙሉ በሙሉ ወደተግባር ገብቶ እስኪሰራበት ድረስ በአይቲ ክፍል የሠራተኞችን ስራ ተክቶ እንዲሰራ በማድረግ ሠራተኛውን የማላመድ ስራ ተሰርቷል፡፡
- ቴክኖሎጂው ለሠራተኛው ቀጣይ ህይወት የተሻለ እና ተፈላጊነትን የሚጨምር መሆኑን በማስረዳት የትግበራው ተባባሪ እንዲሆን በማድረግ ተሰርቷል፡፡
- ሠራተኛው በቴክኖሎጂ እንዲጠቀም እና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ላይ ብልሽት እንዳያደርስ መቆጣጠር የሚያስችል አይሲቲ ፖሊሲ (ICT Policy) እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

### 2.1. የተተገበሩ እና ለሌሎች ተሞክሮ የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎች

ድርጅቱ በጊዜ ሂደት እና በተለያዩ ምዕራፎች በድርጅቱ አሰራር ላይ ከፍተኛ ውጤትና መሻሻልን ሊያመጡ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተግባራዊ በማድረግ አመራሩም ሆነ ሠራተኛው በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ረገድ የተሻለ እንዲሆን ከማድረግ በተጨማሪም ስራዎችን በተቀላጠፈ፣ በፍጥነትና ወጪን በቆጠበ ሁኔታ በመጠቀም የተሻለ የሀብት አሰባሰብ ስርዓት እንዲፈጠር በማድረግ የድርጅቱን እድገት ወደተሻለ አቅጣጫ እንዲመራ ያስቻለ ሲሆን ድርጅቱም ቴክኖሎጂን የማስተዳደርና የመምራት ከፍተኛ ልምድ አካብቶበታል፡፡ ይህም ድርጅቱ ለራሱ ከመጠቀም አልፎ ለሌሎች ተቋማት በቂ ተሞክሮ ለመስጠት በሚያስችለው ደረጃ ላይ እንዲገኝ አስችሎታል፡፡ ስለሆነም በድርጅቱ የተተገበሩና ለሌሎች ተቋማት ተሞክሮ የሚሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

#### 2.1.1. ሲሲቲቪ ካሜራ (CCTV Camera)




### 2.1.1.1. የቴክኖሎጂው ማብራሪያ

- ድርጅቱ በግቢው ውስጥ የሚደረጉ አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ወቅቱን የጠበቀ እና ለክትትል የሚመቹ ቴክኖሎጂዎችን እንደ አስፈላጊነታቸው ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ሲሲቲቪም (CCTV) የዚህ አንዱ ተግባር አጋዥ የቴክኖሎጂ መሳሪያ ተደርጎ እየተሰራበት ይገኛል፡፡
- የካሜራውን የትግበራም ሆነ ሙሉ በሙሉ የዝርጋታ ስራው በድርጅቱ ሠራተኞች አማካይነት ያለምንም ተጨማሪ ክፍያ ወጪ የተከናወነ ነው፡፡
- በአሁኑ ሰዓት 16 ካሜራዎች በተመረጡ ቦታዎች ላይ ተተክለው 24 ሰዓት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል፡፡

### 2.1.1.2. ቴክኖሎጂው የሚሰራው ስራ


- በድርጅቱ ውስጥ በተመረጡ ቦታዎች አላስፈላጊ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ይቆጣጠራል፡፡
- በቀረጻ የያዛቸውን መረጃዎች ሪከርድ አድርጎ እስከሚፈለገው ጊዜ ድረስ ያስቀምጣል፡፡
- ሁሉም ሀላፊ በቢሮ ሆኖ እያንዳንዱን እንቅስቃሴ በካሜራው በቀጥታ መመልከት እንዲችል ተደርጓል፡፡

### 2.1.1.3. ቴክኖሎጂው ያመጣው ውጤት

- አላስፈላጊ የሆኑ በግቢው ውስጥ የሚደረጉ የሠራተኛም ሆነ የተገልጋይ እንቅስቃሴን መቆጣጠር ተችሏል፡፡
  - ሆን ተብሎ የሚደረግ የኤሌትሪክ ሀይል በማቋረጥ ስራዎችን ለማደናቀፍ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ማስቀረት ተችሏል፡፡
  - የድርጅቱ ሠራተኞች ሳይሆኑ በግቢው ውስጥ በመግባት በሠራተኛ የገላ መታጠቢያ ገላቸውን ለመታጠብ የሚገቡ የማይታወቁ ሰዎች በመለየት የእርድ ክፍሉን ሀይጅንና ሳኒቴሽን ለመቆጣጠር እገዛ አድርጓል፡፡
  - ሠራተኞች በስራ ሰዓት የሚያደርጉትን በየቦታው ያለስራ መቆም እና መንቀሳቀስ በመግታት ሠራተኛው በስራ ሰዓት በስራ ገበታው ላይ እንዲገኝ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

- በእርድ ክፍል ከዚህ ቀደም አስቸጋሪ የነበሩ የስራ አካባቢዎች ንጽህና በተለይ የእርድ ክፍል ወለል ላይ የነበረን የንጽህና ችግር አሁን ላይ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡
- ከዚህ ቀደም የነበሩ የስርቆት ሂደቶችን እንዲቆም አድርጓል፡፡ ለምሳሌ፡-
  - የሞራ ስርቆት፣
  - በበረዶ ቤት የሚቀመጡ የደንበኞች የሽንፍላ ስርቆት፣
  - በእርድ ክፍል ውስጥ የስጋ መቆረጥ፣
  - በቴክኒክና ጥገና ክፍል የነበሩ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች ብክነትና ስርቆት፡፡

### 2.1.2. ጥሪ ማዕከልና የቲኬቲንግ ሲስተም (Call Center and Ticketing System)




#### 2.1.2.1. የቴክኖሎጂው ማብራሪያ

- ድርጅቱ የነበረውን የደንበኞች የቅሬታ አቀራረብ ሂደት ዘመናዊ ለማድረግ ታሳቢ ተደርጎ የተተገበረ ቴክኖሎጂ ነው፡፡
- 8868 አጭር የመስመር ቁጥርን በመጠቀም ተግባራዊ የተደረገ ነው፡፡

#### 2.1.2.2. ቴክኖሎጂው የሚሰራው ስራ

- ደንበኛው በአጭር ኮድ ደውሎ ጥያቄውን የሚያቀርብበት ሲሆን ጥያቄውን ለኮል ሴንተር ኤጀንት በኩል ቲኬት ተቆርጦለት ሲስተሙ እንዲያስተናግደው ያደርጋል፡፡
- ቴክኖሎጂው ቲኬቲንግ ሲስተም ያለው በመሆኑ ጥያቄው የቀረበበትን ሰዓት፣ ጥያቄው የተላለፈለትን ክፍል እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ይይዛል፡፡
- የቀረበውን ጥያቄም ሆነ ቅሬታ ለሚመለከተው ወይም ችግሩን ለሚፈታ አካል በቀጥታ ያቀርባል (Escalate)፡፡
- ሲስተሙ Service Level Agreement (SLA) ያለው በመሆኑ ችግሩን እንዲፈታ የቀረበለት አካል አፋጣኝ ምላሽ የማይሰጥ ከሆኑ ለቀጣዩ የቅርብ ሀላፊ የቀረበውን ቅሬታ ወይም ጥያቄ እንደገና ያደርሳል፡፡ ችግሩ ተፈትቶ ለደንበኛው ምላሽ እስኪሰጥ ድረስ ሲስተሙ ለቅርብ ሀላፊ ጉዳዩን እያሳወቀ እስከ ድርጅቱ የበላይ ሀላፊ ድረስ በየደረጃው ቅሬታውን እንዲደርስ ከማድረጉም ባሻገር የተሰጠው ምላሽ በ SLA መሆኑ ሪፖርት ያደርጋል፡፡





- ሀላፊዎችንም ሆነ ሠራኞችን በስልካቸው ለማግኘት የግድ ቢሮ መቀመጥ ላይኖርባቸው ይችላል፡፡ ሲስተሙ በመስመር የተደወለን ስልክ ወደሞባይላቸው እንዲዞር አድርጎ ባሉበት ቦታ ማግኘት እንዲቻል በማድረግ አስቸኳይ መረጃዎችን በወቅቱ እንዲደርሳቸው አስችሏል፡፡
- እያንዳንዱ ሠራተኛ ሲስተሙን በመጠቀም ያለምንም ክፍያ በግቢው ውስጥ በሞባይል እርስ በእርስ ማገናኘት ያስችላል፡፡ ይህም ቴክኖሎጂውን ከመጠቀም ባሻገር ሠራተኛው ለኢትዮ ቴሌኮም የሚከፍለውን ወጪ ይቀንስለታል፡፡
- የአገልግሎት እርካታን ለመለካት በደንበኛው ቤት እየዞሩ የሚደረገውን እንግልት በማስቀረት በደንበኛው ስልክ ቁጥሮች ላይ መጠየቂያዎችን በመላክ ደንበኛው መልስ እንዲሰጥ በማድረግ የደንበኛን የአገልግሎት እርካታ ቀጥታ ሲስተሙ ያለሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ራሱ ለክቶ (Automatic Survey) ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡ ይህም የደንበኛ የእርካታ መጠንን ተአማኒነት ከፍ ያደርገዋል፡፡



- ደንበኞች የሚያቀርቡትን ጥያቄዎችን እና ቅሬታዎች መነሻ በማድረግ ተመሳሳይነት ያላቸውን ጥያቄዎች አንድላይ በመሰብሰብ ያደራጃል፡፡ ይህም ሲስተሙ የራሱ የሆነ Knowledge system ያለው መሆኑ፣
- እያንዳንዱን የደንበኛውን ጥያቄም ሆነ ቅሬታ ሪከርድ አድርጎ የሚይዝ በመሆኑ እንደገና ለመስማት እና ለትንተና የሚያስፈልግ ከሆነ ቅጅውን ማስቀረት ይቻላል፡፡

ዐ፤




- ልክ እንደደንበኛው ሁሉ ሠራተኛውም ቅሬታ ካለው በዚህ ሲስተም ተጠቅሞ ማቅረብ እንዲችል ተደርጎ ተደራጅቷል፡፡

## 2.1.2.3. *ያመጣው ውጤት*

- ደንበኛው ያለምንም የሰዓት ገደብ (24 ሰዓት) ጥያቄውንም ሆነ ቅሬታውን ማቅረብ እንዲችል አድርጓል፡፡
- ችግሩን እንዲፈታ የቀረበለት የሚመለከተው አካል ችግሩን ለመፍታት የወሰደውን ጊዜ ሲስተሙ የሚመዘግብ በመሆኑ የተጠያቂነት አሰራር እንዲፈጠር አስችሏል፡፡
- የእርካታን ደረጃ ሲስተሙ በራሱ መገምገም የሚያስችለው በመሆኑ ያለምንም ሶስተኛ ወገን አስፈላጊነት አሊያም ጥናት አድራጊ ሳያስፈልገው በራሱ ልኬቱን መስራት እንዲችል አድርጓል፡፡
- ሠራተኛው ሲፈለግ በግቢው ውስጥ እስከሆነ ድረስ በቢሮ ባይኖር እንኳን በሞባይሉ ላይ ተደውሉ ማግኘት እንዲቻል አድርጓል፡፡
- ደንበኛው ያለምንም መሰላቸት እና የወረቀት ጋጋታ ሳይኖር በአጭሩ ያለውን የእርካታ መጠን እንዲገልጽ አስችሏል፡፡
- ቅሬታ እንዲፈቱ የቀረበላቸው አካላት ቅሬታው ከቀረበበት ሰዓት ጀምሮ ሲስተሙ መቁጠር የሚጀምር በመሆኑ ከሌላው ጊዜ በተለየ ፍጥነት የደንበኞች ቅሬታ በፍጥነት እንዲፈታ አስችሏል፡፡

## 2.1.3. GPS and Fuel Management system









## 2.1.3.1. የቴክኖሎጂው ማብራሪያ

- ድርጅቱ የተሽከርካሪዎቹን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠርና በተገቢው ሁኔታ የአገልግሎት አሰጣጡ የተሻለ እንዲሆን ለማስቻል አስፈላጊነታቸው የታመነባቸውን ቴክኖሎጂዎች እያጠና ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ከዚህም አንዱ ጂፒኤስ (GPS) ቴክኖሎጂ ነው፡፡
- የድርጅቱን ተሽከርካሪዎችና የነዳጅ አጠቃቀም ችግር ለመፍታት ታሳቢ ተደርጎ የተተገበረ ቴክኖሎጂ ነው፡፡
- ብዙ ድርጅቶች በአብዛኛው ቴክኖሎጂውን በክላውድ (Cloud) ስለሚጠቀሙ ለሚጠቀሙበት ኪራይ የሚከፍሉ ሲሆን የድርጅታችን ለየት የሚያደርገው በራሱ ሰርቨር ላይ የተገጠመ በመሆኑ ኪራይ አይከፍልም፡፡

## 2.1.3.2 ቴክኖሎጂው የሚሰራው ስራ

- እያንዳንዱን ተሽከርካሪ የወጣበት መስመር፣ የሹፌሩ ስም፣ ደርሶ የመጣበት ኪሎ ሜትር፣ ያለው ነዳጅ፣ የተጓዘበት ፍጥነት የመሳሰሉትን መረጃዎች በደንብ አጠናክሮ ይይዛል፡፡
- የተሽከርካሪውን ታሪክ (ከመነሻ እስከ መጨረሻ) ያስቀምጣል፡፡ ይሄ መረጃ እስከተፈለገበት ጊዜ ድረስ በሲስተሙ ይዞ ይቆያል፡፡
- የተሽከርካሪውን የነዳጅ አጠቃቀሙን መቆጣጠር ያስችላል፡፡
- ነዳጁ መቼ ተሞላ፣ ምን ያህል መጠን ተሞላ፣ ምን ያህል ተጉዟል፣ ምን ያህል ሊትር ነዳጅ ይቀራል፣ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች በግልጽ ያስቀምጣል፡፡
- ነዳጁ ተሽከርካሪው እንቅስቃሴ ሲያደርግ ከተገመተው በላይ የነዳጅ መጉደል ሲያጋጥም በቀጥታ ሲስተሙ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

### 2.1.3.3. ቴክኖሎጂው ያመጣው ውጤት

- ቴክኖሎጂው ከተተገበረ በኋላ ከደንበኞች ይቀርብ የነበረን የስርጭት ፍጥነት ቅሬታ ተቀርፏል፡፡
- አላስፈላጊ በሆኑ የስርጭት መስመር ላይ የተሽካርካሪዎችን መገኘትና ከተመደቡበት መስመር ውጪ የሚደርጉትንእንቅስቃሴ መቆጣጠር የተቻለ በመሆኑ ይሄንን ችግር አስቀርቷል፡፡
- በተሽከርካሪው ላይ የሚደርሱ ስርቆትም ሆነ ጉዳቶች መቆጣጠር ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡-
  - ባትሪ ሲነቀል
  - ነዳጅ ከታሰበው በላይ የሆነ መጠን ሲጎድል
  - ያለአግባብ ማሽከርከርና ፍሬን መያዝ
  - ፍጥነት ከተገደበው በላይ ሲንቀሳቀስ
- መረጃው በCloud ላይ ቢሆን ኖሮ ሊቆይ የሚችለው ቢበዛ ለ6 ወር ብቻ ነበር፡፡ ሆኖም ድርጅቱ በራሱ ሰርቨር ላይ አድርጎ የሚጠቀም በመሆኑ መረጃውን ድርጅቱ እስከፈለገበት ጊዜ ድረስ ማቆየት ከማስቻሉም በላይ መረጃው በሶስተኛ ወገን ቁጥጥር ውጪ እንዲሆን አስችሎታል፡፡
- የነዳጅ ፍጆታን እና ስርቆትን ለመቆጣጠር አስችሏል፡፡
- ለድርጅቱ አመራር ለውሳኔ አሰጣጥ የሚረዱ በርካታ ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡

## 2.1.4. የመረጃ ማዕከል(Data Center Management)

### 2.1.4.1. የቴክኖሎጂው ማብራሪያ

የድርጅቱ የሲስተምም ሆነ የቴክኖሎጂ መረጃዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆኑ ለማስቻል ታሳቢ ተደርጎ የተዋቀረ ነው፡፡

### 2.1.4.2. ቴክኖሎጂው የሚሰራው ስራ

- መረጃዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
- አስፈላጊውን የመረጃ ቋት መያዝ እንዲችል ሆኖ የተሟላ እና ደረጃውን የጠበቀ ነው፡፡
- በቂ ሰርቨሮች ያሉት በመሆኑ መረጃዎች በበቂ ሁኔታ መያዝና ለተፈለገው ጊዜ ማከማቸት የሚያስችል ነው፡፡
- Fire wall የተገጠመ በመሆኑ የመረጃዎች ደህንነት እንዲጠበቅ አድርጓል፡፡





- የድርጅቱን ኮምፒውተሮች በጠቅላላ በኔትዎርክ በማደራጀት እያንዳንዱን ኮምፒውተር ከማዕከል በመሆኑ መቆጣጠር እና መከታተል ተችሏል፡፡ ይህም ከዚህ በፊት ኮምፒውተር ላይ የሚጫኑ እና የሚከለከሉ መረጃዎችን በየኮምፒውተሩ ላይ ሄዶ ይሰራ የነበረውን በማዕከል በማድረግ የጊዜና የጉልበት ብክነትን ከማስቀረቱም ባሻገር የቁጥጥር ስርአቱን ከፍ አድርጎታል፡፡



## 2.1.4.3. *ያመጣው ውጤት*

- የድርጅቱ መረጃዎች በአስተማማኝ ደህንነት ላይ እንዲገኙ አስችሏል፡፡
- በኢንተርኔት አማካይነት ከውጭ ወደድርጅቱ የሚገቡ መረጃዎች ከተፈቀደው መረጃ ውጪ እንዳይገባ የተደረገ በመሆኑ ከውጭ የሚመጡ እና ድርጅቱ የማይጠቀምባቸው አላስፈላጊ ሳይቶችን በመገደብ የመረጃ ጥቃትን (Cyber Attack) ለመቀነስ አስችሏል፡፡
- ሁሉም ኮምፒውተር የሚጠቀም ሠራተኛ ኮምፒውተሮችን ከማዕከል መቆጣጠር የተቻለ በመሆኑ አላስፈላጊ የሆኑ ሳይቶችን ማየት እንዳይችል መከታተልና መቆጣጠር ተችሏል፡፡ በመሆኑም በዚህ ችግር ተጠምደው የነበሩ ሠራተኞች አላስፈላጊ መረጃዎችን በመመልከት የሚያባክኑትን የስራ ሰዓት መቀነስ አስችሏል፡፡
- እያንዳንዱ ሠራተኛ ከኢንተርኔት ላይ የሚያወርዳቸው (Download) መረጃዎች ምን ምን እንደሆኑ፣ ለምን ያህል ጊዜ እንዳወረዳቸው፣ የትኛው ሳይቶችን እንደተጠቀመ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች የሚይዝ ከመሆኑም ባሻገር ለመገደብ የሚያስችል የመቆጣጠሪ ቴክኖሎጂ አለው፡፡
- ሠራተኛው እየተጠቀማቸው ያሉ የበየነ መረብ መረጃዎች ሪፖርት ያደርጋል፡፡




## 2.1.5. ERP (Enterprise Resource Planning)

### 2.1.5.1. የቴክኖሎጂው ማብራሪያ

- ድርጅቱ የሚጠቀምበት ዌብ ቤዝድ ኢንተግሬትድ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም አሁን ዘመኑ የደረሰበትና ለማስተዳደርም ሆነ ለመጠቀም ቀላልና አመቺ የሆነ የቴክኖሎጂ አማራጭ ነው፡፡
- ድርጅቱ ውስጥ የሚገኙሁሉም የስራ ክፍሎችም ሆኑ የስራ እንቅስቀሴዎች በአንድ በተቀናጀ የመረጃ አሊያም የሲስተም ስርዓትስር እንዲሰበሰብ እና አንዱ ክፍል ከሌላው ክፍል በሲስተም አማካይነት እንዲናበብ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ሲስተም ነው፡፡
- በዚህ ሲስተም ሁሉም የስራ ክፍሎች እንዲተሳሰሩ ከማድረግ በተጨማሪም መረጃዎችን በሲስተም አንዱ ሲስተም ከሌላው ቅብብሎሽ በማድረግ የመረጃ ስርጭትን ወቅታዊና ፈጣን ከማድረጉም ባሻገር ለአመራሩ ፈጣን ውሳኔ እንዲሰጥ ለማድረግ የሚያግዝ የሲስተም ስርዓት ነው፡፡

### 2.1.5.2. የሚሰራው ስራ

ሲስተሙ 11 ሞጁሎችን ታሳቢ አድርጎ የሚሰራ ሲሆን እነዚህም


#### i. System Adminstration

ሲስተም አድሚን ወይም ሲስተም ማናጀር ከማዕከል ሆኖ ሌሎች ሞጁሎችን የሚቆጣጠርበት እና የሚያስተዳድርበት ነው፡፡


#### ii. Human resource management

ይህ የሰው ሀይል አስተዳደር በአጠቃላይ የሚያደርጋቸውን የስራ እንቅስቃሴዎች የሚያሳልጥ ሲስተም ነው፡፡ ይህም ሲስተም ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ


- የሠራተኛውን አጠቃላይ ሙሉ መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፡፡




- በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙ በመዋቅር የተፈቀዱ የስራ መደቦችን የያዘ ሲሆን ተሟልቷል ወይም አልተሟሉም የሚለውን መረጃ ያሳያል፡፡





- የሠራተኛውን የዓመት እረፍት አደራጅቶ ምን ያህል እረፍት እንዳለው በራሱ በማስላት ያስቀምጣል፡፡ ወደኋላ የሶስት ዓመት ፈቃድ አስልቶ ይሰራል፡፡




- ሠራተኛው የዓመት ፈቃድ ሲጠይቅ በሲስተም እንዲስነሳ ያደርጋል፡፡
- ከቅጥር ማስታወቂያ ጀምሮ እስከ መጨረሻው የቅጥር ደብዳቤ ድረስ ስራውን መስራት ያስችላል፡፡
- የሠራተኛውን የስራ አፈጻጸምን መረጃ በየጊዜው ይይዛል፡፡




- አጠቃላይ በህብረት ስምምነት ላይ የሚገኙ የቅጣት ህጎች በሲስተም የገቡ በመሆናቸው እርምጃ በሚወሰድበት ወቅት ሲስተሙን በመጠቀም ብቻ ደብዳቤ ማውጣት የሚያስችል ሲሆን ይህንንም መረጃ ለቀጣይ አደራጅቶ ይይዛል፡፡





### iii. Clinic management


ለህክምና ክሊኒክ የሚቀርቡ ሠራተኞች የህክምና ካርድ እንዲያወጡ ያደርጋል፡፡ ያለውን የቀድሞም ሆነ አዲስ የህክምና መረጃም በሲስተሙ ላይ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

### iv. Fleet and maintenance management

ይህ ሲስተም ተሽከርካሪዎችን እና ማሽነሪዎችን  የጥገና ፍላጎት ማስነሻ እና ጥገናው በተፈለገው ወቅት መሰራቱን መከታተል የሚያስችል ሲሆን እያንዳንዱ ተሽከርካሪም ሆነ ማሽነሪ በሚጠገንበት ወቅት በስራው ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎች ስብጥርና የሙያ ድርሻ የወሰደው የስፔር ፓርት እና የመሳሰሉትን መዝግቦ የሚይዝ የሲስተም ክፍል ነው፡፡

- የጥገና ስራ ትዕዛዞችን (Work Order) በሲስተም በማስነሳት ለሚሰራው አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡




- እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ምን ያህል ስፔር ተጠቀመ፣ በስራው ላይ ምን ያህል ሠራተኛ ተሳተፈ፣ ሠራተኛው የነበረው አስተዋጽኦ ምን ያህል ነበር የሚለውን መረጃ አቀናጅቶ ያሳያል፡፡
- ተሽከርካሪው ምን ያህል ተጓዘ፣ ምን ያህል ነዳጅ ፈጀ፣ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች አሟልቶ ይይዛል፡፡

Addis Ababa Abattoirs Enterprise


**Machineries/Vehicles Spare Parts & Fuel Consumption**

**Date From 1/11/2013 To 30/4/2014**

| | FUL | SIV | Total |
|---|---|---|---|
| 03-00439-AA | 6,021.60 | 22,762.11 | 28,783.71 |
| 03-00440-AA | 57,413.64 | 4,500.00 | 61,913.64 |
| 03-00441-AA | 9,333.48 | 38,362.85 | 47,696.33 |
| 03-04130-AA | 625.32 | 5,031.14 | 5,656.46 |
| 03-11194-AA | 60,933.96 | 44,718.37 | 105,652.33 |
| 03-11195-AA | 57,459.96 | 4,782.61 | 62,242.57 |
| 03-11196-AA | 23,576.88 | 300.00 | 23,876.88 |
| 03-13519-AA | 393.72 | 0.00 | 393.72 |
| 03-13520-AA | 90,161.88 | 11,595.30 | 101,757.18 |
| 03-13755-AA | 0.00 | 8,624.54 | 8,624.54 |
| 03-21053-AA | 56,788.32 | 702.68 | 57,491.00 |
| 03-21054-AA | 60,540.24 | 11,335.76 | 71,876.00 |
| 03-21055-AA | 13,386.48 | 400.00 | 13,786.48 |
| 03-21056-AA | 49,122.36 | 5,182.61 | 54,304.97 |
| 03-22565-AA | 52,480.56 | 200.00 | 52,680.56 |
| 03-22566-AA | 60,262.32 | 1,963.66 | 62,225.98 |
| 03-22567-AA | 45,463.08 | 10,649.78 | 56,112.86 |
| 03-22568-AA | 48,126.48 | 0.00 | 48,126.48 |
| 03-38111-AA | 13,015.92 | 1,070.08 | 14,086.00 |

## v. Finance management

- ለክፍያ የሚቀርቡ መረጃዎች ሙሉ በሙሉ መረጃዎችን ክፍያ ከሚጠይቁ ክፍሎች በሲስተም የሚቀርብ ሲሆን ፋይናንስ የማረጋገጥ ስራውን በመስራት ክፍያ እንዲፈጽም ያመቻቻል፡፡
- በዱቤ የተሸጡ ሽያጮችና ያልተሰበሰበ እዳ ካለ እንዲሁም ድርጅቱ መክፈል ሲገባው ያልከፈለው ክፍያ ካለ ምን ያህል ገንዘብ፣ ከማን መሰብሰብ ወይም ለማን መክፈል እንዳለበት፣ ምን ያህል ጊዜ እንደቆየ እና ሌሎች መረጃዎችን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡
- በድርጅቱ ሂሳብ መካከል እና ባንክ ባለው ሂሳብ መካከል ያለውን ልዩነት ለመከታተል የሚረዳ በባንክ በሚመጣ ባንክ ስቴትመንት ቀጥታ ለሲስተሙ በመስጠት (Import) በማድረግ ከድርጅቱ የሂሳብ መዝገብ ጋር በማመሳከር ሲስተሙ በራሱ Bank reconciliation ይሰራል፡፡




- የደመወዝ፣ የጥቅማጥቅም፣ የትርፍ ሰዓት እና ሌሎች ሠራተኛው ሊያገኛቸው የሚገቡ ክፍያዎችን ሲስተሙ በራሱ አስልቶ ያስቀምጣል፡፡




- የድርጅቱን የፋይናንስ ሪፖርቶችን በሚፈለገው ሰዓት ሰርቶ የድርጅቱን ትርፍና ኪሳራ ማወቅ ያስችላል፡፡

## vi. Property Management

- እንዲገዙ ወይም ከንብረት ክፍል ወጪ እንዲሆኑ የሚጠየቁ ንብረቶችን እንዲጠየቁ የሚያደርግ ሲሆን ለማስፈቀድም የሚመለከተው አካል በዚሁ ሲስተም ፈቃድ መስጠት (Autorize) እንዲችል ያደርጋል፡፡
- እንዳንዱ የግዥ ሂደት የት እንደደረሰ፣ ማን ጋር እንደቆየ እና የመሳሰለውን መከታተል የሚያስችል መከታተያ አለው፡፡ በዚህም በሂደት ላይ ያሉ እንዲሁም ተገዝተው የገቡ ንብረቶችንም ማየት ያስችላል፡፡

የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት
Addis Ababa Abattoirs Enterprise

**Purchase Request Accomplishment All**

**አቶ ዮሐንስ በላቸው ደምሴ**

| S.No | PRV No | PR Date | Assign Date | Duration from PR Date | Performs Date | Duration from Assign Date | POV | POV Date | Total Duration from PR |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 49 | PRV001-034213 | 13/5/2013 | 3/6/2013 9:03:44 | 20 | 3/6/2013 9:05:32 | 0 | POV001-001792 | 3/6/2013 12:08:18 | 20 |
| 50 | PRV001-034187 | 5/5/2013 | 3/6/2013 9:08:15 | 29 | 3/6/2013 9:08:34 | 0 | POV001-001818 | 12/6/2013 8:28:23 | 37 |
| 51 | prv001-034240 | 24/5/2013 | 28/5/2013 9:19:18 | 3 | 4/6/2013 9:23:07 | 6 | POV001-001787 | 4/6/2013 12:08:51 | 10 |
| 52 | PRV001-034236 | 28/5/2013 | 4/6/2013 12:16:16 | 6 | 4/6/2013 12:17:13 | 0 | POV001-001796 | 4/6/2013 12:21:53 | 6 |
| 53 | prv001-034312 | 8/6/2013 | 9/6/2013 9:53:12 | 1 | 9/6/2013 9:53:38 | 0 | POV001-001824 | 15/6/2013 12:00:08 | 7 |
| 54 | prv001-034309 | 8/6/2013 | 9/6/2013 9:38:18 | 1 | 9/6/2013 9:58:23 | 0 | | | 351 |
| 55 | prv001-034313 | 8/6/2013 | 9/6/2013 9:57:12 | 1 | 9/6/2013 9:57:17 | 0 | POV001-001825 | 15/6/2013 12:41:54 | 7 |
| 56 | prv001-034183 | 4/5/2013 | 8/6/2013 1:58:33 | 33 | 8/6/2013 1:58:36 | 0 | POV001-001808 | 8/6/2013 2:08:33 | 35 |
| 57 | PRV001-034262 | 28/5/2013 | 10/6/2013 11:32:20 | 12 | 10/6/2013 11:32:38 | 0 | | | 391 |
| 58 | prv001-034222 | 18/5/2013 | 11/6/2013 11:58:58 | 23 | 11/6/2013 11:37:02 | 0 | POV001-001822 | 12/6/2013 3:40:38 | 24 |
| 59 | prv001-034122 | 11/5/2013 | 11/6/2013 4:34:44 | 0 | 12/6/2013 4:34:38 | 1 | POV001-001823 | 12/6/2013 4:39:01 | 1 |
| 60 | prv001-034232 | 21/5/2013 | 16/6/2013 1:45:28 | 25 | 16/6/2013 1:54:41 | 0 | POV001-001834 | 18/6/2013 10:06:03 | 27 |
| 61 | prv001-034325 | 12/6/2013 | 16/6/2013 12:40:45 | 4 | 17/6/2013 8:55:13 | 1 | POV001-001829 | 17/6/2013 8:55:58 | 5 |
| 62 | prv001-034333 | 12/6/2013 | 15/6/2013 11:01:38 | 3 | 17/6/2013 8:57:35 | 2 | | | 377 |

- እያንዳንዱ የድርጅቱ ንብረት የትኛው ሠራተኛ ጋር እንዳለ የሚያሳይ ሲሆን በተጨማሪም እያንዳንዱ ንብረት የተገዛበት ዋጋ እና አሁን ላይ ያለው ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ የእርጅና ተቀናናሽ (Depreciation) በመስራት ስሌቱን ያስቀምጣል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት
Addis Ababa City Administration Office, Addis Ababa Abattoirs Enterprise
Fixed Asset Allocated to Employee

08935 — የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት

አቶ ቴዎድሮስ ከተማ በላይነህ — ሲኒየር የአይሲቲ፣ የቢሮ ማሽን ጥገናና የኔትወርክ ባለሙያ

| Issue Date | FIV No | F.A. Code | Item ID | Item Name | Amount | SIV | Descr |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1/11/2009 | FIV000738 | 015-07-00112 | 1610000016 | COMPUTER | 8,096.00 | - | Fixed Asset Valuation |
| 1/11/2009 | FIV000741 | 015-01-00194 | 1610000016 | COMPUTER | 10,920.00 | - | Fixed Asset Valuation |
| 1/11/2009 | FIV000746 | - | 16100000361 | Floor Cleaner | 7,800.00 | - | Fixed Asset Valuation |
| 1/11/2009 | FIV000747 | 015-06-00014 | 16100000007 | FILE CABINET | 7,740.00 | - | Fixed Asset Valuation |
| 19/6/2013 | FIV001364 | - | 1610000367 | AIR CONDISHNER | 36,277.00 | SIV001-06110 | - |
| 25/1/2013 | FIV001647 | 016-01-0711-0712 | 1610000104 | APC BACK UPS 650V A-1600VA | 10,892.16 | 10609 | - |
| 5/4/2014 | FIV001687 | 015-09-0750 | 1610000582 | LCD MONITOR 19 inch | 5,482.75 | SIV001-06180 | - |

## vii. Slaughtering management

ይህ ሲስተም ድርጅቱ እየሰጠ ያለውን ዋነኛ የእርድ አገልግሎት ለማሳለጥ ይረዳ ዘንድ ሁሉንም ከእርድ አገልግሎትና ተያያዥ ጉዳዮች አንጻር ያለውን መረጃ በሲስተም በማደራጀት ወቅታዊ መረጃ እንዲኖርና ከእርድ አገልግሎት አንጻር ድርጅቱ ያለበትን ወቅታዊ የእቅድ አፈጻጸም ለመከታተል ያስችላል፡፡

- ለእርድ የቀረቡ እንስሳትን የቅበላ ሂደት በሚከናወንበት ሰዓት በሲስተም መዝግቦ ይይዛል፡፡ የቅበላ ሠራተኞች ያልተቀበሉት እንስሳት የእርድ አገልግሎት ክፍያ እንዳይከፈልበት ይቆጣጠራል፡፡

Addis Ababa City Administration Office,
Addis Ababa Abattoirs Enterprise
የከብት ቅበላ ሪፖርት/Cattles Receiving Report
18/6/2014 - Addis Ketema

SLAUGHTERING FEE OXEN

| SL No | Customer Name | Rec. | Paid | Diff |
|---|---|---|---|---|
| 3 | ABREHAM MISGANU | 7 | 6 | 1 |
| 45 | ADDIS KETEMA K.K..K..04 R.CLUB | 8 | 7 | 1 |
| 48 | IDEGET BETREMARIAM | 2 | 2 | 0 |
| 52 | FIKADU TEMAME | 1 | 1 | 0 |
| 66 | GETACHEW KEBEDE G/MICHAEL | 1 | 1 | 0 |
| 75 | ABIDELO KEBEDE | 2 | 2 | 0 |
| 76 | badeg getiro g/mariam | 3 | 3 | 0 |
| 83 | TENSU G/MARIAM | 4 | 4 | 0 |
| 86 | WORKU URUGA ADLA | 1 | 1 | 0 |
| 88 | BADEGE ASEFA | 1 | 1 | 0 |
| 92 | SIYOUM H/MARIYAM G/TSADIK | 2 | 2 | 0 |
| A1 | Edegte tsefa hulgbe he/se/mahebre | 9 | 9 | 0 |
| A101 | HIGUA LIGA | 4 | 4 | 0 |
| A107 | GINBARU SINBIT ARGAW | 5 | 5 | 0 |

- እርድ የተከናወነባቸው እንስሳት የውስጥ ብልቶች በሃኪም ምርመራ ውጤት መሰረት ያለፉና የወደቁትን በሲስተም እንዲገባ ያደርጋል፡፡ ይህንን ውጤት ለደንበኛው እንዲደርስ ሠርተፍኬት ያዘጋጃል፡፡



በአዲስ አበባ ከተማ ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት
ብልት ማስረከቢያ ቅፅ / Caracas Distribution Voucher
SLAUGHTERING FEE OXEN
18/6/2014 1st Round

171 ደረሰኝ ቁጥር፡ AA-CaSI01757891-Kolfe 1 Normal

የደንበኛው ስም፡ GENET FEKEDE ክ/ከተማ፡ ቡራዩ ቀበሌ፡ 01 የቤት ቁጥር፡ 583 ስልክ፡ 0911242009/0913422908 የማከፋፈያ መስመር፡ Kolfe የእርድ ቁጥር፡ 171 የሒሳብ ቁጥር፡ 12659 እርድ ክፍል፡ የክርቲያን እርድ ክፍል/Christian Room በተሽከርካር መለያ ቁጥር፡ ______________ የአገልግሎት ክፍያ ፈጽመው ያስረከቡት/ዋቸው ከብት/ቶች ወይም በግ/ጎች ታርደው ሥጋውን/ቸውን የሥጋ አስረካቢ ሃላፊ በሆኑት 02410 - አቶ ሱልጣን ኑረዲን መሐመድ አማካይነት እንደሚከተለው ተልከዋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥጋው ዓይነት | ብዛት | የሚሠራጭ | የወደቀ | በረዶ ቤት ያለ የተቀመጠ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሥጋ | 1 | 1 | 0 | 0 % |
| 2 | ጉበት | 1 | 0 | 1 | 0 % |
| 3 | ምላስ | 1 | 1 | 0 | 0 % |
| 4 | የጭንቅላት ሥጋ | 1 | 1 | 0 | 0 % |
| 5 | ኩላሊት | 2 | 2 | 0 | 0 % |
| 6 | ልብ | 1 | 1 | 0 | 0 % |
| 7 | ሣንባ | 1 | 1 | 0 | 0 % |
| 8 | ጨጓራ | 1 | 1 | 0 | 0 % |
| 9 | ሸንፍላ | 1 | 1 | 0 | 0 % |


ደንበኛው/ተወካዩ ሲረከብ የተከሰተ ጉድለት ፤ ብልሽት ወዘተ ካለ አስተያየት




- የእርድ አገልግሎት ክፍያ ሲከፈል የእንስሳው መረጃ ለተለያዩ ክፍሎች አስፈላጊውን መረጃ ለማሟላት አሊያም መረጃውን ማወቅ ለሚፈልጉ ግልጽ ለማድረግ እንዲቻል ሲስተሙ ያሰራጫል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ለእርድ ክፍል ለመታረድ አስፈላጊውን ማሟላቱን እና የብልት ማስረከቢያ ሰነድ ላይ መረጃዎች ማስገባት እንዲያስችል፤
- ለፋይናንስ ክፍል የተከፈለውን የገንዘብ መረጃ በመያዝ የገባውን የገቢ መጠን፤
- ለማርኬቲንግ ክፍል የቆዳና ሌጦ የኪሎ መረጃ ለማስገባት እንዲያስችል

- ለገቢዎች የእርድ ደንበኞች ምን ያህል እንስሳትን በድርጅታችን እንዳሳረዱ አስፈላጊውን መረጃ አደራጅቶ የሚይዝ በመሆኑ በሚፈለግበት ወቅት ወዲያውኑ ፕሪንት አድርጎ መስጠት ያስችላል፡፡



Addis Ababa City Administration Office, Addis Ababa Abattoirs Enterprise
Customers Slaughtering Summary
Report Range: 1/4/2014 To 25/6/2014 / 12/10/2021 To 3/04/2022

To ______________________ Subcity Small Tax Payers Branch Office


Addis Ababa
Customer: SHOA SHOPPING CENTER — Line: Muslem
Zone: [illegible] — Woreda: 03 — H.No: 004 — TIN: 0000083152

| | | | [illegible] | [illegible] | [illegible] | Total Summary |
|---|---|---|---|---|---|---|
| M21 | 89190 | Quantity | 24 | 63 | 40 | 127 |
| | | Sub Total | 24 | 63 | 40 | 127 |
| p78 | 78249 | Quantity | 15 | 27 | 52 | 94 |
| | | Sub Total | 15 | 27 | 52 | 94 |
| | | Grand Total | 39 | 90 | 92 | 221 |


[illegible]

## viii. Budget Management

- ዓመታዊ የበጀት መረጃዎችን በመደበኛም ሆነ በካፒታል ለይቶ ያስቀምጣል፡፡
- እያንዳንዱ የበጀትም ሆነ የካፒታል እቃ ግዥ በዓመታዊ እቅዱ ላይ ከተቀመጠው ውጪ እንዳይሆን ይቆጣጠራል፡፡
- የተጠየቀው በጀት እጥረት ያለው ከሆነም የበጀት ዝውውር ካልተደረገ በስተቀር በዘፈቀደ ወጪ እንዳይደረግ ይገድባል፡፡
- ድርጅቱም ሆነ የስራ ክፍሎች የተጠቀሙትን በጀት በሚፈለገው የጊዜ ገደብ ለይቶ ያስቀምጣል፡፡




- ድርጅቱ በዋናነት በበጀት ዓመቱ ሊሰራ ያቀዳቸውን ስራዎች መነሻ በማድረግ በየወሩ ከፋፍሎ ያስቀምጣል፡፡ በተመሳሳይም አፈጻጸሙንም በዛው ልክ የሚያስቀምጥ በመሆኑ እቅድና ክንውኑን ማነጻጸር ያስችላል፡፡




## ix. Production management

- የተመረቱ ምርቶችን መረጃ ያስቀምጣል፡፡
- የእርድና የምርት ስራዎችን ግብዓት ላይ ከዋሉ ከጥሬ እቃ፣ ከሰው ሀይል፣ ከኤሌትሪክና ከውሀ ፍጆታ እና ከመሳሰሉት አንጻር መረጃዎችን በመውሰድ ኮስት በራሱ አስልቶ ያስቀምጣል፡፡



Production Cost Management

| | Date |
|---|---|
| Select | 24/6/2014 |
| Select | 23/6/2014 |
| Select | 22/6/2014 |
| Select | 21/6/2014 |
| Select | 20/6/2014 |
| Select | 19/6/2014 |
| Select | 18/6/2014 |
| Select | 17/6/2014 |
| Select | 16/6/2014 |
| Select | 15/6/2014 |

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10 ... >>

Total Batches: 11 Process: 16:06:00

| | Item ID | Description | Unit | Quantity | Cost Status |
|---|---|---|---|---|---|
| Select | 90000007 | AKAK SLUGTHERING COST በግ | PCS | 3.00 | False |
| Select | 90000008 | AKAK SLUGTHERING COST ፍየል | PCS | 41.00 | False |
| Select | 90000009 | AKAK SLUGTHERING COST ግመል | PCS | 7.00 | False |
| Select | 90000003 | AKAK SLUGTHERING COST [illegible] | PCS | 409.00 | False |
| Select | 41254 | Aorta Tube | PCS | 2,982.00 | False |
| Select | 30 | CATTLE BILE | KG | 0.00 | False |
| Select | 10 | DOG MEAL | KG | 600.00 | False |
| Select | 3180000015 | FEET(HOOVES) | PCS | 0.00 | False |
| Select | 418 | GOAT AND SHEEP PENIS COUSTMER | KG | 0.00 | False |
| Select | 23 | GOAT AND SHEEP SMALL INTESTINE | PCS | 831.00 | False |
| Select | 417 | GOAT AND SHEEP TESTICLE COUSTMER | KG | 0.00 | False |
| Select | 90000014 | HIDE AND SKIN COST(GOAT SKIN) | PCS | 530.00 | False |
| Select | 90000002 | HIDE AND SKIN COST(OXE HIDE) | PCS | 3,852.00 | False |
| Select | 90000013 | HIDE AND SKIN COST(SHEEP SKIN) | PCS | 301.00 | False |
| Select | 600 | Leg Tenedon | PCS | 14,820.00 | False |
| Select | 28 | OXE HIDES HEAD | PCS | 3,848.00 | False |
| Select | 36 | OXE PENIS | PCS | 3,404.00 | False |
| Select | 22 | OXE SMALL INTESTINE | PCS | 3,848.00 | False |
| Select | 280 | OXEN TESTICLE AAAE | KG | 380.50 | False |
| Select | 21 | RAW HOOVES | PCS | 14,820.00 | False |
| Select | 41286 | REJECTED LEAVER | PCS | 30.00 | False |
| Select | 3180000022 | SELECTED HORN | PCS | 5.00 | False |
| Select | 90000005 | SLUGTHERING COST በግ | PCS | 299.00 | False |
| Select | 90000006 | SLUGTHERING COST ፍየል | PCS | 489.00 | False |
| Select | 90000010 | SLUGTHERING COST [illegible] | PCS | 3.00 | False |
| Select | 90000012 | SLUGTHERING COST ጥጃ | PCS | 1.00 | False |
| Select | 90000001 | SLUGTHERING COST [illegible] | PCS | 3,239.00 | False |
| Select | 1003100005 | Stomach | PCS | 0.00 | False |
| Select | 3180000007 | SWISHER HAIR | KG | 0.00 | False |
| Select | 3180000004 | TALLOW | KG | 0.00 | False |

### x. Archive management

- የድርጅቱ ወጪም ሆነ ገቢ ደብዳቤዎች ስካን በማድረግ ዲጂታላይዝድ እንዲሆን ተደርጎ ተሰርቷል፡፡

### xi. Marketing Management

- ሽያጭ የተከናወነባቸውን መረጃዎች ከነመጠናቸው እና ከነገንዘባቸው በግልጽ ያስቀምጣል፡፡
- ከምርት ክፍል የተረከባቸውን የምርት ዓይነቶች በመጠን ማየት የሚያስችል በመሆኑ የተመረተውን እና የተሸጠውን ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡

## 2.1.5.3. ሲስተሙ ያመጣው ውጤት

- ቀደም ሲል የነበረ ሳይከፈልባቸው አገልግሎት ይሰጥባቸው የነበሩ አሰራሮችን ሙሉ በሙሉ አስቀርቷል፡፡ በዚህም ድርጅቱ ያጣው የነበረ ገቢን እንዲያገኝ አስችሏል፡፡
- ከዚህ በፊት የነበሩ የማኑዋል አሰራርን ወደሲስተም የተቀየረ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የወረቀት ብክነትን አስቀርቷል፡፡
- አጠቃላይ ከዚህ በፊት የነበሩ ለስራ የሚያስፈልጉ ፎርማቶችን እና የወረቀት ህትመቶችን በማስቀረት በሲስተም እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡
- የደንበኞችን የእርድ መረጃ በቀጥታ በቲን ቁጥር በማውጣት ለገቢዎች ሲስተም በሚያመች መልኩ በማዘጋጀት መረጃውን ይሰጣል፡፡ በዚህም መረጃው በትክክል ደንበኛው ያሳረደውን መረጃ ሲስተሙ የሚሰጥ በመሆኑ እና የመጨመርና የመቀነስ ስራ መስራት የማይቻል በመሆኑ ከተማውን ከዚህ ዘርፍ ማግኘት የሚገባውን የግብር መጠን በትክክል እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡
- የየእለቱን የእርድ አገልግሎት፣ የምርት ሽያጭ፣ የገቢ ሁኔታ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች በማንኛውም ሰዓት ማየት የሚቻል በመሆኑ የድርጅቱን እንቅስቃሴ ለመገምገም ያስችላል፡፡



- የሠራተኛ ዓመታዊ ፈቃድ ጋር ተያይዞ ቀድሞ ስራው የሚሰራው ማኑዋል በመሆኑ ይሰሩ የነበሩ አላስፈላጊ የሠራተኛን ፈቃድ የመጨመርና የመቀነስ ክፍተቶች እንዲቆሙ ተደርገዋል፡፡
- ሠራተኛው የሰዓት መቆጣጠሪያ በመታወቂያ በባርኮድ ይመታ የነበረ ቢሆንም አንዳንድ ሠራተኞች የሌላን ሠራተኛ መታወቂያ በመያዝ እየመቱ ያስቸገሩ በመሆኑ አሁን ላይ በዓይን እና በጣት አሻራ እንዲመቱ በማድረግ ክፍተቱ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡




- አብዛኛው ህጋዊ ሠነዶች ሁሉ በዲጂታል እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡
- በድርጅቱ ውስጥ የሚደረጉ ማንኛውም ፋይናንሻል፣ ኦፕሬሽናል እና ሌሎችም ሪፖርቶችን በሙሉ በተፈለገው ጊዜ የተፈለገውን መረጃ ሲስተሙ በአጭር ጊዜ ውስጥ መስጠት ያስችላል፡፡

## 3. ማጠቃለያ

ድርጅቱ የተገበራቸው ቴክኖሎጂ እና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ሳይቆራረጥ ማስቀጠል ዋነኛ ዓላመው ሲሆን በቀጣይ በተተገበሩት ቴክኖሎጂዎች ተሞርኩዞ እና ተጨማሪ ቴክኖሎጂዎችን በማካተት ሀገሪቱ አሁን እየተከተለችው ያለውን ቴክኖሎጂ መር የአሰራር ስርዓት በመተግበር ድርጅቱን ወደላቀ ደረጃ በማሸጋገር የደንበኞችን ቅሬታ ሙሉ በሙሉ በመቅረፍ ድርጅቱን ትርፋማ ለማድረግ ይሰራል፡፡

በቀጣይ ድርጅቱ እንደ እቅድ የያዘው የከተማውን እቅድ እስከ ፈጻሚ የማውረድ ስራዎች እንዲተገበሩና ሲስተም እንዲበጅለት የማድረግ ስራ ሲሆን ማንኛውም የተቋሙ የስራ እንቅስቃሴ በመረጃ ቋት ውስጥ እንዲመዘገብ በማድረግ የአመራሩንና የሠራተኛውን የስራ አፈጻጸም ሲስተሙ በራሱ እንዲለካ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በፊት ይፈጠር የነበረውን የስራ አፈጻጸም አሞላል ቅሬታ ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ ታሳቢ ተደርጓል›› የፋይናንስ ሪፖርት በአለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝ ስታንዳርድ (IFRS) መሠረት ሲስተሙ በራሱ እንዲያዘጋጅ በማድረግ የድርጅቱን የውጭ ኦዲት ወቅታዊ ለማድረግና ለማዘመን በቁርጠኝነት ለመስራት በቀጣይ ታቅዷል፡፡

ስለሆነም ሌሎች መሰል ተቋማት ድርጅቱ ተግባራዊ ያደረጋቸውን የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን እንደ ተሞክሮ መውሰድ የሚቻል ሲሆን በተመሳሳይም ሌሎች ቴክኖሎጂን የሚጠቀሙ ተሞክሮዎችን በመውሰድ እና በመቀመር የድርጅቱን አሰራር የማሻሻል ሂደት ቀጣይነት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሶስት፡- የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አኳያ የተከናወኑ ተሞክሮዎች

## ክፍል አንድ

### 1.1. መግቢያ

ለውይይት መነሻ ይሆናል ተብሎ የቀረበው ይህ የተሞክሮ ሰነድ በቅድሚያ የደብረብረሃንን ታሪካዊ ዳራና ወቅታዊ ሁኔታ ባጭሩ ይዳስሳል፡፡ ደብረብርሀን ከተማ በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ በ1446 የተቆረቆረችና የ600 ዓመት የእድሜ ባለፀጋ ከተማ ነች፡፡ ደብረብርሃን ከተማ ከባሕር ጠለል በላይ 2,700 ሜትር ከፍታ ላይ ትገኛለች፡፡ የቦታውም አቀማመጥ 86 በመቶ ሜዳማ፤ 10 በመቶ ዳገታማ፣ አራት በመቶ ተራራማ የሆነ እና ከዚህም ውስጥ 95 በመቶ ለግንባታ ምቹ የሆነ ቦታ ነው፡፡ የከተማዋን አየር ንብረት ስንመለከትም በቀዝቃዘማ አየር ንብረት ብትታወቅም አሁን ላይ ቀዝቃዛነቱ እየቀነሰ የመጣ፤ በአማካይ 14.5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሙቀትና 964 ሚሊ ሜትር አመታዊ የዝናብ መጠን ያላት ከተማ ነች፡፡

ይህችን የፍቅር ከተማ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሲመሰርቷት በነበራት የቦታ አቀማመጥ ፋይዳ፣ የታሪክ አበርክቶ፣ አየሯ ለጤና ተስማሚ በመሆኑና ብዙ ጥቅምና አገልግሎት ወደፊት ትሰጣለች ብለው በማሰባቸው እንደነበር በስፋት ይነገራል፡፡ ከተማዋ በውስጧና በዙሪያዋ በርካታ የተፈጥሮ ገፀበረከቶችን፤ ብዙ ቅርሶችን የያዘች፣ ለሀገራችን የፖለቲካ እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረከቱ መሪዎችን ያፈለቀች፣ ህዝቧንና ከባቢዋን በሰላምና በጤና ያኖረች እድሜ ጠገብ ትልቅ የሀገር ባለውለታ ከተማ እንደሆነች ከብዙ የታሪክ ድርሳናት መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም የካበተ የእድሜ ዘመኗ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ሆና አገልግላለች፡፡ታላላቅ የሀገር መሪዎች፣ ጥበበኞች፣ ፈላስፎች፣ አርበኞች ወዘተ ፈርተውባታል፡፡

ይሁንና ደብረበርሃን ከተማ እድሜዋና እድገቷ ተቃራኒ ሆኖ በርካታ አመታት አልፈዋል፡፡ በተለይ ደግሞ ከአስር ዓመት በፊት የነበረው ሁለንተናዊ ጉዞዋ ይህን የሚያሳይ እንደነበር ከተማዋን በቅርብ የሚያውቋት ሁሉ ይመሰክረሉ፡፡
ይህ በእንዲህ እንዳለ ከተማዋ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ያለፈውን የኋሊት ጉዞ በመቅበር ያንቀላፋችበትን ጊዜ ለማካካስ እየታተረች ትገኛለች፡፡ ከተማዋ በአሁኑ ወቅት የኢንቨስትመንት መዳረሻ ከተማ በመሆኗ የባለሃብቶች ፍሰትና የህዝቧ ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ፣ አገራዊ ፋይዳቸው የጎላ የሆነ የኢንቨሰትመንት ዘርፎች መዳረሻ እየሆነች መጥታለች፡፡ እድገቷ እየተፋጠነ የበርካታ ኢንዱሰትሪዎች ማእከል የመሆን ግስጋሴ ላይ ትገኛለች፡፡

ኢንቨስትመንት ቃሉ እንግሊዝኛ ሲሆን አሁን አሁን ግን በአማርኛ ሥነ ጽሑፍም በጣም እየተለመደ በመምጣቱ የአማርኛውን አቻ ቃል ማለትም “መዋዕለ-ንዋይ” የሚለው መጠሪያ እስከሚዘነጋ ድረስ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን በየእለቱ ይነገራል፡፡ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት አዋጅም ሳይቀር መዋዕለ ንዋይ ከማለት ይልቅ ኢንቨስትመንት የሚለውን ቃል ሙሉ በሙሉ ተጠቅሟል፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ አንባቢውን ግራ ላለማጋባት ሲባል በዚህ የተሞክሮ ሰነድ ኢንቨስትመንት የሚለውን ቃል ለመጠቀም ተገደናል፡፡ የዚህ ሰነድ ዓለማ ለምን መዋዕለ-ንዋይ የሚለው ቃል ኢንቨስትመንት እየተባለ ተጠራ የሚለው ጉዳይ ባይሆንም አገር በቀል መጠሪያዎችን መጠቀም እንድንለምድና እንድናዳብር አስተያየት ለመጠቆም ነው፡፡

በዚህ የተሞክሮ ሰነድ ውስጥ የተሞክሮ ቅመራዉ አላማ፣ ተሞክሮውን የመቀመር አስፈላጊነት፣ተሞክሮ ሊወሰድባቸው የተመረጡ የትኩረት መስኮች/ወሰን/፣ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ትግበራ ሂደት፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ ለቀጣይ ትኩረት ሊሰጣቸውና ትምህርት ሊወሰድባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ተካተውበታል፡፡

## 1.2. ተሞክሮውን የመቀመር አላማዎች

### ሀ/ ጥቅል ዓላማ

ይህን የተሞክሮ ሰነድ የመቀመር ዋነኛው አላማ በደብረብርሃነ ከተማ በኢንቨስትመንት ዘርፍ የተገኘውን ስኬትና ውጤትን በመሰነድና በማመላከት ወደ ሌሎቹ የኢተዮጵያ እህት ከተሞች እንዲስፋፋ በማድረግ ውጤቶችን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚደረገውን ጉዞ ማፋጠን ነው፡፡

### ለ/ ዝርዝር አላማ

ይህ የተሞክሮ ሰነድ ከላይ በጠቀስነው ዋና አላማ ላይ ተመርኩዞ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፡፡ እነዚህም፡-

- የተሞክሮ ሰነዱ ለትምህርትና ለግንዛቤ ፈጠራ ተግባራት እንዲያገለግል ማስቻል፤
- የደብረብረሃን ከተማ በርካታ ኢንቨስተሮችን በመሳብ ረገድ እያሳየች ያለው አርአያነት የጎላ በመሆኑ ይህንን መልካም ልምድ በመቀመር ለሌሎች ከተሞች ማድረስና ተሞክረውን ለማስፋት፤
- የከተማ አስተዳደሮች በኢንቨስትመንት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግና በከተማቸው ኢንቨስትመንትን በመሳብ እንዴት ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ለመጠቆም፤
- በደብረብረሃን ከተማ አስተዳደር የኢንቨስትመንት ትግበራ ወቅት ያጋጠሙትን ችግሮችና የተፈቱባቸውን አግባብ እንዲሁም የተገኙ ጠንካራ ጎኖችን በቀጥታ ከሌሎች ከተሞች ጋር ለማስተሳሰርና ለመጠቀም፤
- የተገኘውን ተሞክሮ መነሻ በማድረግ አቻ ከተሞች እራሳቸውን በማስተዋወቅና መልካም ስም በመፍጠር ኢንቨስትመንትን ወደየከተማቸው በመሳብ የከተማቸውን ኢኮኖሚ በማሳደግ የሥራ ፈጠራን ማስፋፋት፡፡

## 1.3. ተሞክሮውን የመቀመር አስፈላጊነት

የደብረብረሃን ከተማ አስተዳደር በኢንቨስትምነት ዘርፍ ያስመዘገበውን የላቀ አፈፃፀም ወደ ሌሎች እህት የኢትዮጵያ ከተሞች በተሞክሮነት እንዲስፋፋ በማድረግ በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች በርካታ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ባለሃብቶች ሀብታቸውን ኢንቨስት እንዲያደርጉ ማስቻልና የሀገሪቷን የኢኮኖሚ እድገት ማፋጥን፡፡

## 1.4. መነሻ ሁኔታዎች/ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች

ደብረብርሃን ከተማ ካስቆጠረችው ረጅም ዘመን አንፃር ሲነፃፀር ያስመዘገበችው እድገት እዚህ ግባ የማይባል ነበር፡፡ ምንም እንኳ ደብረብርሃን ከተማ ለአዲስ አበባ ከተማ ቅርብ፣ የአየር ንብረቷ ለስራ ተስማሚ፣ ሰላሟ የተረጋገጠና በቂ የሰው ሀይል ያላት ከተማ ብትሆንም በተሰራባት የፖለቲካ ሴራ ለዘመናት ምንም አይነት የእድገት ለውጥ ሳታሳይ ኖራለች፡፡ ደብረብረሃን ከተማ በግራኝ አህመድ፣ ጣሊያን፣ ደርግ አና ኢህአዴግ ዘርፈ ብዙ መከራ፣ ችግር፣ ሰቆቃና እንግልት ደርሶበታል።

በተለይ ደግሞ የህዋሀት አገዛዝ አካባቢው በኢኮኖሚ እንዳይበለፅግ ጭቆና ያሳድርበት ስለነበር የደብረብርሃን ከተማ የእድገት ጉዞም በእጅጉ የተንቀረፈፈ እንደነበር የከተማው ነዋሪ ያየውና የኖረው መራራ ሀቅ ነው፡፡ ህዋሀት ደ/ብርሀን ከተማ በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ወደኋላ እንድትመለስ፣ ታሪኳ እንዲቀበርና እንዲጠፋ በመሰረታዊነት አቅዶና አልሞ በመስራት ትኩረት የሌላት ከተማ ለማድረግ ያልተወጣው ዳገትና ያልተወረደው ቁልቁለት አልነበርም፡፡ የሴራው አስከፊነት ከአካባቢው መሪ እንዳይወጣ ማድረግ፣ ወደ አካባቢው ኢንቨስትመንት እንዳይመጣ መከልከል፣ የአካባቢው ህዝብ በህይወት እያለ እንደሌለ በማድረግ የትየለሌ ግፍና በደል መፈፀምንም ያካተተ ነበር፡፡ ደብረብርሃን ከተማ በፖለቲካዉ ረገድ ከማእከልነት ወደ ክላኤ ጠረፍነት እንድትቀየር ሆነ። በኢኮኖሚውም የእርዳታ ጥገኛ እስከመሆን የደረሰ የኢኮኖሚ ማሽቆልቆል ተከሰተ። በማህበራዊ ዘርፍ መሰረተ ልማት ተደራሽነት እጅግ አነስተኛ ሽፋን ተሰጠው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የከተማዋ የቅርብ ዓመታት ጉዞ ያለፈውን የኋሊት ጉዞ በመቅበር የሀገራችን የኢንቨስትመንት ማዕከል በመሆን ላይ ትገኛለች። የኢንቨስትመንት ፍሰቷና ተመራጭነቷ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ነው። አሁን ላይ ደብረብርሃን ከተማ የበርካታ ኢንዱስትሪዎች ማዕከል ሆናለች። ለዚህ ደግሞ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች በምክንያትነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ከሀገሪቱ መዲና አዲስ አበባ በቅርብ ርቀት መገኘቷ፤

- ከተማዋና አካባቢዋ ለኢንቨስትመንት ዘርፍ ሰፊ አማራጭ ስላላት፤
- የማኅበረሰቡ ሰፊ የልማት ጥያቄና ራሱም የሠላሙ ጠባቂ መሆኑ፤
- የጉልበት ሰራተኛ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኝባት ከተማ መሆን፤
- ለኢንቨስትመንት አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶች መሟላታቸው፤
- ቀልጣፋ የሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ መኖሩ፤
- የከተማ አስተዳደሩ በተቀናጀ መንገድ ችግሮችን መፍታቱ እና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

## 1.5. ተሞክሮ ሊወሰድባቸው የተመረጡ የትኩረት መስኮች /ወሰን/

ይህ የተሞክሮ ቅመራ ሰነድ የሸፈነው የደብረብርሃን ከተማ ስኬታማ ኢንቨስትመንት አፈፃፀምን ሲሆን በዋናነት ደግሞ የተቀላጠፈ አገልግሎት አሰጣጥ፣ ቅንጅታዊ አሰራር፣ የመሬት አቅርቦት፣ የመሰረተ ልማት ችግር አፈታት፣ ክትትልና ድጋፍ አሰጣጥና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ለሌሎች አቻ ከተሞች ተሞክሮውን ማካፈል ነው፡፡

## 1.6. ተሞክሮውን ለመቀመር የተሄደበት አግባብ

ይህን የተሞክሮ ሰነድ ለመቀመር የሚከተሉትን የአሰራር ስልቶች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

- በደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር የኢንቨስትመንት መምሪያ ስር ያሉ የአራቱም ክለስተር አስተባባሪዎች የየራሳቸውን ክለስተር አስመልክቶ ሙሉ መረጃ እንዲያቀርቡ ከተደረገ በኋላ መረጃዎቹ በዚህ የተሞክሮ ሰነድ እንዲካተቱ ተደርጓል፤
- ተዛማጅ የሆኑና ሌላ መድረክ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉ የኢንቨስትመንት መምሪያ ያዘጋጃቸው ሰነዶችን፣ በኢንቨስትመንት ዙሪያ የተዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ህጎችን በግብዓትነት በመጠቀም፤
- በደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት መምሪያ አማካኝነት የተዘጋጁ የተለያዩ ሪፖርቶች፣ የምርምር ስራዎች፣ የስልጠና ማንዋሎች፣ ቃለ ጉባኤዎች እና ሌሎች የመምሪያው ሰነዶች ለዚህ የተሞክሮ ቅመራ ሰነድ በዋቢነት አገልግለዋል፤
- በአጠቃላይ የተሰባሰቡ ግብዓቶችን መሰረት በማድረግ ትንተና ተካሂዶ ይህ የተሞክሮ ሰነድ ተቀምሯል፡፡

# ክፍል ሁለት፡- የዝግጅት ምዕራፍ

2.1. በከተማው ባለሃብቶች ኢንቨስት እንዲያደርጉ የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር በመፍታት ረገድ በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑ ተግባራት

የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት መምሪያ ባለሃብቶች በከተማው ኢንቨስት እንዲያደርጉ የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር በመፍታት ረገድ በዝግጅት ምዕራፍ የሚከተሉትን ተግባራት ሲያከናውን ቆይቷል፡-

- የከተማ መሬት በመጠኑ በጣም ውስን ለልማት ያለው አሰተዋጽኦ ደግሞ በጣም ወሳኝ ከመሆኑ ጋር ተያያዞ ያለውን መሬት ከማንኛውም አይነት ሁከት ነፃ አደርጎ 501 ሄክታር መሬት ለኢቨስትመንት ዝግጁ ማድረግ፤
- የመሠረተ ልማት አውታሮች አገልግሎት /ቴሌ፣ ውሃ፣ የአሌክትሪክ ኃይል እና መንገድ/ ማሻሻል፣
- የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትምንት መምሪያ ከደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ጥናት በማድረግ ከተማዋ ለኢንቨስትመንት ያላትን ገፀ በረከቶች መለየት፤
- የሰው ሀይል ወይም ጉልበት ገበያ ሁኔታ (ስራ አጥነት፣ የሰው ሀይል ወይም ጉልበት አቅርቦትና ፍላጎት) መለየትና ለኢንቨስተሮች ይፋ ማድረግ፤
- የከተማውን ሰላም ባሰተማማኝ ሁኔታ ለማረጋገጥ ከፀጥታ አካላት ጋር ብዙ የምክክር መድረኮች ተካሂደዋል፡፡ የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር ወቅታዊ ሀገራዊ የፀጥታ ችግርን በግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የከተማው ነዋሪ አከባቢያቸውን ከወትሮ በተለየ መልኩ እንዲጠብቁ ስምሪት ሰጥቷል። ከዚህም በተጨማሪ በየደረጃው ህግ የማስከበር ሥራዎችን ለመሥራት በምልመላና በሥልጠና አቅምን በመገንባት ጠንካራ የሚሊሻ ኃይልን በማሰልጠንና የደንብ ልብስ በማልበስ በየክፍለ ከተማው ስምሪት ሰጥቷል።

የመንግስት ሰራተኛውን የመፈፀም ብቃት ማሳደግ በተለይ፤ በአገልግሎት ጥራትና ቅልጥፍና የተላበሰ፤ ተልኮውን ያወቀ፣ ስራና ሀገር ወዳድ የሆነ፣ ተጠየቂነትንና ሀላፊነትን አምኖ የሚቀበልና በስነምግባሩ የተመሰገነ ባለሙያ ለመፍጠር የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፤

በደብረብርሃን ከተማ ላይ ያሉትን የኢንቨስትመንት አማራጭ በበራሪ ወረቀቶች፣ በብሮሸሮች፣ በማህበራዊ ሚድያ (በዋናነት በደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር የኢንቨስትመንት መምሪያ የፌስቡክ ገፅ አማካኝነት)፣ በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችና የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር ደብረብርሃንን በጋራ እናልማ በሚል የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

- በደብረብርሃን ከተማ ኢንቨስት ለማድረግ የሚመጡ ባለሃብቶች ቅድሚያ ሊያሟሏቸው ስለሚገቡ ዝርዝር ጉዳዮች የያዘ ወረቀት ፕሪንት አድረጎ ማዘጋጀት፤

# ክፍል ሦስት፡- የትግበራ ምዕራፍ

## 3.1. የከተማዋ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ትግበራ ሂደትና የተገኙ ውጤቶች/ተሞክሮዎች

### 3.1.1. የደብረብርሃን ከተማ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ትግበራ ሂደት

ኢንቨስትመንት የአንድ ሀገርን ዘርፈ ብዙ እድገት ማፋጠን ረገድ ላቅ ያለ ሚና እንዳላው በርካታ የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ታዳጊ አገሮች ኢንቨስትመንትን በማሳደግ ገቢና ሥራን ማስፋት ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪም በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በአስተዳደር ዕውቀት የሀገር ውስጥ የግሉ ዘርፍ ኢንተርፕራይዞችን እንቅስቃሴ በማጠናከር ለልማት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ማቅረብ ይችላሉ። ደብረብርሃን ከተማም ይህን የኢንቨስትመንት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በመገንዘብ ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ በመፍጠርና በርካታ የኢንቨስትምንት አማራጮችን በመጠቀም ፈጣን እድገት እያስመዘገበች ያለች ከተማ ነች፡፡ በዚህም መሰረት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የትግበራ ሂደት የሚከተሉትን ቁልፍ ተግባራት ያካተተ ነበር፡፡

የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት መምሪያ ያለፉትን አመታት ተሞክሮ በመቀመር በሰራቸው ማሻሻያዎች መሰረት ባሁኑ ጊዜ ባለሃብቶች የሚጠበቅባቸውን መስፈርት አሟልተው ከቀረቡ ከአንድ እስከ ሁለት ቀን ባለ ጊዜ ውስጥ መሬት አስረክቦ የሚጨርስበትን ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፤

- ወደ ደብረብርሃን ከተማ እየመጡ ያሉ ኢንቨስተሮች ቁጥራቸው እየበዛ ስለመጣ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማፋጠንና እንግልትን ለመቀነስ ሲባል ካሉት መደበኛ የስራ ቀናት በተጨማሪ ቅዳሜና እሁድም ጭምር ባለጉዳዮች እየተስተናገዱ ናቸው፤
- በደብረብርሃንና አካባቢው ያሉትን ገፀ በረከቶች በግብዓትነት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች እንዲስፋፉና እና እርስ በእርሳቸውም ተመጋጋቢ እንዲሆኑ በስፋት ተሰርቷል፡፡ ለምሳሌ፡- የቢራ ፋብሪካ፣ የጠርሙስ ፋብሪካ፣ የብቅል ፋብሪካና የመሳሰሉት ፋብሪካዎች የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት በመጠቀም ለራሳቸውም የመጓጓዣ ወጪ ይቀንሳሉ ለአካባቢው ማህበረሰብም የገቢ ምንጭ በመፍጠር ላይ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በከተማዋ የሚገኙት አብዛኞቹ

ኢንዱስትሪዎች በአምራች ዘርፉ የተሠማሩና እርስ በእርሳቸው ተመጋጋቢ እንዲሆኑ በሰፊው ተሰርቷል፡፡ ይህም ከውጪ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን በመተካት የመዳዳዣ ወጪን እና የምንዛሬ እጥረትን ይቀንሳሉ፡፡

ጥሩ ስምና ዝና ያላቸውን የተመረጡ ባለሃብቶች በከተማ አስተዳደሩ ጥሪ ተደርጎላቸው ኢንቨስት እንዲያደርጉ በመደረጉ በተለያዩ ዘርፎች ግንባታ ላይ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ሀይሌ ገብረስላሴ (ባለ 5 ኮከብ ሆቴል)፣ በላነህ ክንዴ (የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ)፣ አስራትና መንገሻ (የሴንቼሪ ሞል ባለቤቶች) (የብረት ማቅለጫ ፋብሪካ)፣ ወርቁ አይተነው የነዳጅ ዲፖ ግንባታ እና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

- በአራት ዘርፍ ማለትም ምግብና ፋርማሲዩቲካል፣ እንጨትና ብረታ ብረት፣ ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት እና ጨርቃጨርቅና አልባሳት ዘርፍ ለሚሳተፉ የኢንዱስተሪ ክላስተር ተዘጋጅቶና መሬት ተከልሎ የተቀመጠ ስለሆነ ባለሃብት ሲመጣ በመሬት ምርጫና ማቅረብ ስራ የሚጠፋ ጊዜ እንዳይኖር ተደርጓል፤

### 3.1.2. የተገኙ ውጤቶች/ተሞክሮዎች

በደብረብርሃን ከተማ ያለው ከፍተኛ የሆነ የኢንቨስትመንት ፍሰት የሚከተሉትን ገፀበረከቶች አስገኝቷል፣

- ባለ ኮከብ ሆቴል ግንባታና የሪልስቴት ፍላጎት አሁንም በእጅጉ ጨምሯል፣
- የተለያዩ የግልና የመንግስት ባንኮች፣ ኢንሹራንሶች ተስፋፍተዋል፣
- የከተማ አስተዳደሩ የገቢ የመሰብሰብ አቅም አድጓል፣
- የመሠረተ ልማት ግንባታ ተስፋፍቷል፣
- ለበርካታ ወጣቶች የስራ እድል ተፈጥሯል፤በዚህም ወጣቶች ለስደት እንዳይዳረጉ ሆነዋል፡፡
- የዜጎች የኑሮ ደረጃ መሻሻል እንዲያሳይ አድርጓል፣
- ቴክኖሎጂ እና ክህሎት ዳብሯል፤
- ጊዜንና ጉልበትን ቆጣቢ የሆነ የአመራረት ዘዴ ዳብሯል፣
- ዓለም አቀፍ ንግድ እንዲሰፋና እና የውጪ ምንዛሬ እንዲገኝ አድርጓል፣
- ብዙ ዋጋ ያላቸው ሸቀጦች እና አገልግሎቶች ለአካባቢው ማህበረሰብ ገበያ ላይ ውለዋል፡፡

## 3.2. በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር እጅግ የላቀ የኢንቨስትመንት አፈፃፀም የመጣው ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ሆኖለት አይደለም፡፡ ይልቁንም በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ እጅግ ውስብስብና ፈታኝ የሆኑ ሀገራዊና አካባቢያዊ ችግሮችን በጥበብና በብልሃት በመፍታት ነው፡፡ እነዚህም በትግበራ ወቅት የጋጠሙ ችግሮች እንደሚከተለው ውጫዊና ውስጣዊ ተብለው በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡

### ሀ/ ውጫዊ ችግሮች

- በኢንቨስትመንት ዙሪያ የሚዘጋጁ ፖሊሲዎችና መመሪዎች ወጥነት አለመኖር፣
- ሀገራዊና ወቅታዊ ሁኔታዎች፡፡ በሀገሪቱ እየተስተዋለ ያለው የፀጥታ ችግር ባለሃብቶች ገንዘባቸውን እንደፈለጉ ኢንቨሰት እንዳያደርጉ አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን ደብረብርሃን ከተማ ካሁን በፊት የፀጥታ ችግር አጋጥሟት

ባያውቅም በክልሉ ብሎም በሀገሪቱ ጠቅላላ የተከሰተው የሰላም መደፍረስ ምክንያት አንዳንድ ባለሀብቶች ኢንቨስት ከማድረግ ይልቅ ገንዘባቸውን ይዘው ማመንታትን እንዲመርጡ አስገድዷቸዋል፡፡

- ለፕሮጀክቶች የብድር ጥያቄ አበዳሪ ተቋማት አፋጣኝ ምላሽ ያለመስጠት፡፡ የብድር አገልግሎት መገኘት አለመቻሉ ኢንቨስትመንቱ በሚፈለገው መንገድ እንዳይፈፀምና እንዳያድግ ከሚደርጉት ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡
- የውጪ ምንዛሬ እጥረት መኖር፡፡ ኢንቨስተሮች መዋዕለ ነዋያቸውን ለማፍሰስ ሲያስቡ የሚያዩት የመጀመሪያ ነገር የአገሪቱ መጠባበቂያ የውጭ ምንዛሬ ክምችት ምን ያህል ነው የሚለውን ጉዳይ ነው፡፡

## ለ/ ውስጣዊ ችግሮች

- ምንም እንኳ የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ረጅም ርቀት የተጓዘ ቢሆንም አሁንም ቢሆን በአገልግሎት አሰጣጣችን የተወሰነ ያለመርካት ሁኔታ እየታየ ነው፡፡ በተለይ ከከተማችን መፈጸምና ማስፈጸም አቅም ውስንነት ጋር በተያያዘ አጥጋቢ ምላሽ ያላገኙ ችግሮች አሁንም ብዙ ናቸው፡፡
- በደብረብረሃን ከተማ ካሉ ኢንዱስትሪዎች አብዛኞቹ የሚፈጥሩትን ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ መዲናዋ ወንዞችና ወደ ማህበረሰቡ መልቀቃቸው የአየር ንብረትን ለማስተካከል፣ የብዝሃ ህይወትን ለመጠበቅና ለንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር ፈጥሯል፡፡
- ፋብሪካዎች ለሰራተኞቻቸው የሚከፍሉት ደመወዝ አነስተኛ መሆን፤ አንዳንድ ፋበሪካዎች ለሰራተኞቻቸው በጣም አነስተኛ የሆነ ደመወዝ በመክፈላቸው ምክንያት ሰራተኛው በሚፈለገው ልክ ምርታማ አለመሆን፡፡
- የተወሰኑ ኢንቨስተሮች መሬት ከተሰጣቸው በኋላ ምንም ኢንቨስት ሳያደርጉበት ለረጅም ጊዜ አጥሮ ማቆየት፤
- የመሠረተ ልማት አውታሮች አገልግሎት በተለይም ደግሞ መብራትና መንገድ በሚፈለገው ልክ አለማደጉ፣

## 3.3. ያጋጠሙ ችግሮች የተፈቱበት አግባብ


የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት መምሪያ በኢንቨስትመንት ትግበራ ወቅት ላጋጠሙት ችግሮች መፍትሄ ለማበጀት ሞክሯል፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሉም ችግሮች በከተማ አሰተዳደሩ አቅም ተፈትተዋል ማለት አይደለም፡፡ አንዳንዶቹ ችግሮች (ምሳሌ፡- የውጭ ምንዛሬ እጥረት) እንኳን በከተማ አስተዳደሩ ሊፈቱ ይቅርና እንደሀገርም ትልቅ ፈተና የሆኑ ናቸው፡፡ ስለዚህ በኢንቨስትመንት ትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ማነቆዎች በከተማ አስተዳደሩ አቅም የተፈቱበት አግባብ እንደሚከተለው በዝርዝር ተብራርቷል፡፡

ማንኛውም ኢንዱስትሪ ምርቱን በሚያመመርትበት ወቅት ሆነ ከምርት በሁዋላ የሚለቀውን ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አካባቢን በማይጎዳና ስነምህዳሩን በማያዛባ መልኩ ማስወገድ እንዳለበት የሚደነግግ ህግና መመሪያ ስላለ መመሪያውን ባላከበሩ ፋብሪካዎች ላይ የዞኑ አካባቢ ይበቃ ቢሮ የተለያዩ ቅጣቶችን ማለትም የቃል ማስጠንቀቂያ፣ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ የገንዘብ ቅጣትና ሌሎች መመሪያው የሚፈቅደውን ቅጣቶች እንደየችግሩ አሳሳቢነት በመጣል ችግሩን ለመቀነስ ተሞክሯል፡፡ ለምሳሌ፡- የደብረብርሃን ቆዳና ሌጦ ፋብሪካ በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ የከፋ የጤና እክል ማምጣቱ ስለተረጋገጠ እንዲያስተካክል ማስጠንቀቂያ ተፅፎለት ሊያስተካክል ባለመቻሉ ምክንያት ሊዘጋ ችሏል፡፡

- አነስተኛ የሆነ የደመወዝ አከፋፈልን አስመልክቶ ከደብረብርሃን የስራ እድል ፈጠራና ክህሎት መምሪያ እና ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ ጋር በመተባበር የደብረብርሃን ኢንቨስትመንት መምሪያ አነስተኛ ደመወዝ ከፋይ የሆኑ ፋብሪካዎችን በማወያየት አንዳንዶቹ ወዲያው የደመወዝ ማስተካከያ ሲያደርጉ ሌሎቹ ደግሞ በሂደት የደመወዝ ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል፡፡
- በከተማችን በሚገኙ በተለያዩ ተቋማት የሚታዩትን የመልካም አስተዳደር ችግሮች በየጊዜው በመለየት ለችግሮቹ መፍትሄ ለመስጠት ራሱን የቻለ የመልካም አስተዳደር ዕቅድ በማቀድ ለተለዩ ችግሮች ባለቤት በመስጠትና በአጭር፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜ እቅድ ተለይተው እንዲፈቱ ለማድረግ ጥረት ተደርገዋል፤
- መሬት ወስደው ኢንቨስት ሳያደርጉ ለረጅም ጊዜ መሬት አጥረው የሚያስቀምጡ ባለሃብቶች ላይ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግና ህጋዊ ሂደቱን በጠበቀ መልኩ መሬታቸውን ነጥቆ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ማድረግ ብሎም ለሌላ ሊያለማ ለሚችል ባለሃብት ማስተላለፍ ተችሏል፤

የደብረብርሃን የፀጥታ ሀይል በየደረጃው የሚፈፀሙ ከጥቃቅን እስከ ከባድ ወንጀሎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር ሆነው ወደ ህግ የማቅረብ ሥራውን ተግተው እንዲሰሩና ህ/ቡም ከፀጥታው አባላት ጎን በመቆም የፀረ-ሰላም ኃይሎችን በማጋለጥ በትብብር መንፈስ እየሰሩ ይገኛሉ።

- አንዳንድ የመሰረተ ልማት አለማሟላትን አስመልክቶ የገንዘብ አቅም ያላቸውን ኢንቨስተሮች በማሳመን በራሳቸው አቅም የመንገድ ጠረጋና መብራት ዝርጋታ እንዲያደርጉ ማድረግ ተችሏል፤ ለምሳሌ ዛሙ ኤምዲኤፍ 40 ሚሊዬን ብር ገደማ በማውጣት መብራት በራሱ አቅም ማስገባት ችሏል፣ ሰማህኝ የሪልእስቴት ግንባታ PLC. በራሱ አቅም የመንገድ ጠረጋ አካሂዶ ግንባታ ጀምሯል፤ ምግብ ክለስተር ላይ ያሉ ባለሀብቶች በጋራ ሆነው መንገድ ሰርተው ወደስራ ገብተዋል፣ ቶማስና አረጋሀኝ የተባሉ በብረታብረት ክለስተር ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች መንገድ ገንብተው ወደስራ ገብተዋል፡፡
- በከተማዋ እየመጡ ያሉ አዳዲስ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ መሰማራት የሚፈልጉት ኢንዱስትሪዎችን እርስ በእርሳቸው እና ከነባር ኢንዱስትሪዎች ጋር ተመጋጋቢ እንዲሆኑ በማድረግ ከውጪ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን በመተካት የምንዛሬ እጥረትን መቀነስ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ:- ደብረብርሃን ላይ ያሉ የቢራ ፋብሪካዎች ገብስ ከአርሶ አደሩ፣ ብቅል ከቮልት ማልት የብቅል ፋብሪካ፣ ጠርሙስ ደግሞ ከጁኒፐር የብርጭቆ ፋብሪካ እንዲያገኙና እንዲተሳሰሩ ተደርጓል፡፡ በተጓዳኝ ጁኒፐር የብርጭቆ ፋብሪካ ሰማኒያ ፐርሰንት አካባቢ የሚሆነውን ጥሬ እቃ ከመርሀቤቴ አካባቢ ያገኛል፡፡


መልካም
አስተዳደር

የደብረብርሃን ከተማ ኢንቨስትመንት መምሪያ አሁን ላይ እየተስተዋለ ያለው የኢንቨስትመንት ፍሰት ቀጣይነት ይኖረው ዘንድ በከተማው ለወደፊት የሚሆን የመሬት ዝግጅት እያደረገ ይገኛል፤

የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት መምሪያ ከደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ከአሁን በፊት ከተሰራው ስራ በተጨማሪ በደብረብርሃንና አካባቢው ያሉ ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች በግብአትነት ሊያገለግሉ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን በማጥናትና በመለየት ላይ ይገኛል፤

ባለሀብቶች የፋይናንስ ስኬትን ለማረጋገጥ እና ስማቸውን ለመገንባት የተለያዩ ስልቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ሆኖም ግን የኢንቨስትመንት ትርፋማነት ቀጣይነት የሚኖረው የአካባቢውን ማህበረሰብና ስነ ምህዳር ያልጎዳ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በደብረብርሃን ከተማ ኢንቨስት ያደረጉና ወደፊትም ኢንቨስት ለማድረግ የሚመጡ ባለሃብቶች የማህበረሰቡንና ስነምህዳሩን በማይጎዳ መልክ ስራቸውን እንዲሰሩና ዘመናዊ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት እንዲኖራቸው ከአካባቢ ጥበቃ መምሪያ ጋር በመተባበር የግንዛቤ ስራ በሰፊው እየተሰራ ነው፡፡

## 4.2. ተሞክሮውን ለአቻ ከተሞች /ተቋማት ለማስፋት የተሄደበት ርቀት

የደብረብርሃን ከተማ በኢንቨስትመንት ዘርፍ እያመስመዘገበ ያለውን ላቅ ያለ ለውጥ በርከት ላሉ የሀገሪቱ ከተሞች በተሞክሮነት ለማስተላለፍ ተሞክሯል። ለምሳሌ፡- አፋር ሰመራ ከተማ፣ አዲስ አበባ ከተማ፣ ወራቤ ከተማ፣ ደሴ ከተማ፣ ሰቆጣ ከተማ፣ ደብረማርቆስ ከተማ፣ ፍኖተ ሰላም ከተማ እና ሰሜን ሸዋ ዞን ላሉ ሁሉም የወረዳ ከተሞች በደብረብረሃን ከተማ ያለውን የላቀ የኢንቨስትመንት አፈፃፀም በተለይም ደግመ የተቀላጠፈ አገልግሎት አሰጣጥ፣ ቅንጅታዊ አሰራር፣ የመሬት አቅርቦት፣ የመሰረተ ልማት ችግር አፈታትና ሌሎችም ጉዳዩች ዙሪያ በተለያዩ ጊዜያት ተሞክሮ ለማጋራት ተችሏል፡፡

## 4.3. ማጠቃለያ

### 4.3.1. ትምህርት ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዩች

### ሀ/ በጥንካሬ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችና ትምህርቶች

ፕሮጀክቶች ያሉበትን የትግበራ ሥራ ሂደት የአፈፃፀም ደረጃ ለይቶ በማወቅ፣ ከፕሮጀክቱ ባህሪ (scale, size & complexity) አንፃር በተገቢው የጊዜ ፍጥነት የትግበራ ሂደቱ ስለመከናወኑ መረዳትና የፕሮጀክቱን ችግሮች ለይቶ ማወቅ፣

- ፕሮጀክቶች የጠየቋቸውን አገልግሎቶች ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ወይም ጥያቄዎቻቸው የሚገኙበትን ሁኔታ በማወቅ ለተፈጠሩ ችግሮች ተገቢውን የመፍትሔ እርምጃ መስጠት፣
- በመንግስት ልዩ ትኩረት በተሰጣቸው የሥራ መስኮች ላይ የሚሰማሩ ባለሃብቶች /ፕሮጀክቶች በትግበራ የሥራ ሂደት ስለሚያጋጥሟቸው ችግሮችና ችግሮቹን ለመፍታት ስለሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች በቂ መረጃ አግኝቶ መደገፍና የተለየ ክትትል ለማድረግ፣
- ባለሃብቶች/ ፕሮጀክቶች በትግበራ የሥራ ሂደት አፈፃፀማቸው የሀገሪቱን እና ወይም የክልሎችን የኢንቨስትመንትና ሌሎች ኢንቨስትመንት ነክ የሆኑ ተዛማጅ ሕጎችን ማክበራቸውን እና ግዴታዎቻቸውን መወጣታቸውን በማረጋገጥ በአግባቡ የሚሰሩትን ማበረታታት እና ህገወጥ ስራ የሚሰሩትን ማረም መቻሉ፤
- መሬት ከሶስተኛ ወገን ነፃ አድረጎና በየክለስተሩ ደልድሎ በማስቀመጥ ለመሬት መረጣና ክለስተር ድልደላ የሚጠፍውን ጊዜ መቀነስ መቻሉ፤
- የገንዘብ አቅም ያላቸው ኢንቨስተሮች ለፋብሪካቸው የሚያስፈልገው ነገር ግን የከተማ አስተዳደሩ ማሟላት ያልቻላቸው መሰረተ ልማቶች በራሳቸው አቅም እንዲገነቡ ማግባባትና ማሳመን፣ ለዚህም የእውቅናና ምስጋና ሰርተፍኬት መስጠት መቻል፤
- አዳዲስ እየመጡ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታቸው ለነባር ኢንዱስሪዎች ግብዓት ሊሆን የሚችል ምርት የሚያመርቱ ወይም እነሱ የነባር ኢንዱስተሪዎችን ምርት/ተረፈ ምርት በግብአትንት መጠቀም የሚችሉ እንዲሆኑ አድርጎ በማስተሳሰር ሊገጥማቸው የሚችልን የጥሬ እቃ ብሎም የውጪ ምንዛሬ እጥረት መቀነስ መቻሉ፤

## ለ/ በድክመት የተገኙ ትምህርቶች

የመሰረተ ልማት ስራዎችን በየጊዜው ፍትሃዊነትና ተደራሽነትን በጥናት በመለየት መፍትሄ የሚሰጥ አደረጃጀት አለመኖሩ የተወሰነ የስራ መጓተት ስለፈጠረብን ወደፊት በሰፊው የምንሰራበት የስራ ዘርፍ ነው፤

- መሰረተ ልማት ስራዎችን እነ ቴሌ፣ መብራት ሃይልንና ውሃና ፍሳሽን ሊያስተሳስራቸው የሚችል አደረጃጀት አለመኖሩ የስራ ቅልጥፍናን ያጓትታል፤
- በደብረብርሃን ከተማ ኢንቨስትመንት መምሪያ የግብዓት እጥረት መኖር ለምሳሌ መምሪያው መኪናና ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎች ያለመሟላት፤
- ምንም እንኳ ኢንቨስትመንት ለደብረብርሃን ከተማ እድገት ወሳኝ ቢሆንም በሌላ አባባል የውጭ ምንዛሬ ማምጣቱ፤ የሥራ እድል መፍጠሩ፤ የከተሞች መስፋፋትን ማፋጠኑ ወዘተ በማምጣቱ አስፈላጊነቱ የሚያጠያይቅ ባይሆንም ከአካባቢያዊ ጥበቃ ሥራዎች እንዲሁም ከሰብዓዊ መብት ጥበቃ አንጻር ከፍተኛ የሆነ የቁጥጥር ማነስ አለ፤
- ለሀገራችን ምርቶች ገበያ የማፈላለግና የማስፋት ሥራ ተሰርቷል፡፡ ሆኖም የምርቶችን አቅርቦት በሚፈለገው መጠንና ጥራት እንዲሁም የተወሰኑት እሴት ያልተጨመረባቸው በመሆናቸው የታቀደውን ያህል ውጤታማ አልሆነም፡፡

*የሀብታሞችና የድሆች ፍልስፍና ይህ ነው፤ ባለጠጎች ገንዘባቸውን ኢንቨስት አድርገው በተረፈው ለመኖር ይሞክራሉ። ድሆች ደግሞ በገንዘባቸው ተዝናንተው የተረፈውን ኢንቨስት ለማድረግ ይጣጣራሉ"። (Robert Kiyosaki)*